# የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው

## በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

በተስፋዬ ሮበሌ

ራዕይ አሳታሚ
1991 ዓ.ም. አዲስ አበባ

# የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው

## በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን – ተስፋዬ ሮበሌ

# The Teachings of Jehovah's Witnesses

## as Evaluated/Judged by The Word Of God – Tesfaye Robele

የዘመን አቆጣጠሩ እ. ኢት. አ. (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር) ካልተባለ በስተቀር በጎርጎርዮሳውያን አቆጣጠር ማለት ነው።

የተለየ መግለጫ ካልቀረበ በስተቀር በመጽሐፍ ውስጥ ያሉት ጥቅሶች በ1954 ዓ.ም. በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አሳታሚነት ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።

የሽፋን ሥዕል፦ ሠዓሊ እንየሁ ጸጋዬ ናቸው።

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው። (Copyright C 1999 – Raey Publishers) ያለ አሳታሚው ፈቃድ አባዝቶ ማሳተምም ሆነ የተወሰነ ክፍልን በተለያዩ መንገዶች ማራባት በጥብቅ የተከለከለ ነው። በማንኛውም ዓይነት መልኩ መረጃዎችን ለመውሰድ ከተፈለገ በትክክል ሥርዓቱን ጠብቆ ሊጠቀስ፥ በእግርጌ ማስታወሻዎች ሊመላከት ይገባዋል።

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ. 101539
አዲስ አበባ

RP.04 2M

## ምስጋና [Acknowledgments]

ፍጹም ልሠራ በማልችልበት ጊዜ ይህን መጽሐፍ እንድጽፍ ያስቻለኝና የረዳኝን ልዑል እግዚአብሔርን ከልብ አመሰግናለሁ።

የከበረ ጊዜውን መሥዋዕት በማድረግ ሆሄያቱን በማረም፥ ሰዋሰውን በማስተካከል፥ የረዳኝን ወንድም ምኒልክ አስፋውን እጅግ በጣም አድርጌ አመሰግናለሁ።

እንዲሁም በጸሎትም ሆነ የሚያስፈልገኝን ሁሉ በመርዳት ከጎኔ ለቆሙት፦ ወንድም አስፋው ታደሰና ባለቤቱ እመቤት ዓለሙ፤ የመጽሐፉን የሽፋን ሥዕል ውብ አድርጎ ያዘጋጀውን ሠዓሊ እንየው ጸጋዬን፤ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ መጽሐፍ እንድጽፍ ያበረታታኝን ወንድም ደስታ ደምሴን እንዲሁም የመጽሐፉን ረቂቅ በኮንፒውተር አሳምራ የተየበችውን እኅት መሠረት ዳምጠውን፥ አንዳንድ ጠቃሚ መጻሕፍትን ፎቶ ኮፒ አድርጎ የሰጠኝን ዶክተር አንድሪው ናክ [Dr. Andrew Noch]ን፥ የይሖዋ ምስክሮች በኢትዮጵያ የሚለውን ጽሑፍ እንድጠቀምበት የፈቀደልኝን ዶክተር ስቲቨ ስትራውስ [Dr. Steve Strauss]ን እግዚአብሔር ይባርካችሁ ለማለት እወዳለሁ። **ለሁሉም ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ!**

## የመጽሐፉ መታሰቢያነት

ክርስቶስን የሕይወቴና የሐሳቤ አልፋና ዖሜጋ እንዳደርግ ለአስተማሩኝ፥ በቃልም በተግባርም ምሳሌ ለሆኑኝ አስተማሪዎቼ፡-

- አቶ ዮሴፍ መንግሥቱ
- አቶ ምኒልክ አስፋው
- ሚስተር ጆን እና ሚስስ ሜሪ ካርፔንተር
- ሚስተር እና ሚስስ ኦርተር ማክሌን
- አቶ ለዐከ ታፈሰ
- ዶክተር ብራይን ሆልት

እንዲሁም ብዙ የተማርኩባቸው፥ በክርስቶስ ፍቅር ዘወትር በልቤ ለሚኖሩት የኮልፌ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የጥምቀት፥ የአገልግሎት ሥልጠናና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት (1988 ዓ.ም.–1990 ዓ.ም.) ተማሪዎቼ መታሰቢያ ይሁንልኝ።

## Dedication

This book is dedicated to my teachers who have taught me that Christ is the ALPHA and OMEGA of thought and life:-

- Ato Yosef Mengestu
- Ato Menelik Asfaw
- Mr. John and Mary Carpenter
- Mr. And Mrs. Arthur Mac Lean
- Ato Leake Tafesse
- Dr. Brian Holt

Finally, I would also like to dedicated this book to all of my students from whom I have learned much: Kolfe KHC Bible School (1996-1998) students, in the catechism and Ministry Classes.

## መቅድም

“የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን” የተባለው ይህ መጽሐፍ ክርስቲያኖች መሠረተ እምነታቸው ከእግዚአብሔር ቃል የተቀዳና በአመክንዩ የተደገፈ ለመሆኑ ቃለ እግዚአብሔርን ዋቢ በማድረግ ከመናፍቃን ራሳቸውን እንዲጠብቁ ለማስቻል ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን የይሖዋ ምስክሮችም ይህን መጽሐፍ በጥሞና እንዲመለከቱት አሳስባለሁ።

*የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር* (Watchtower Bible and Tract Society) የሚባለው የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት በ1994 ዓ.ም. “ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር” በሚል ርዕስ 445 ገጽ ያለው መጽሐፍ ለንባብ አብቅቶአል። ይህ መጽሐፍ እንደማንኛውም *‘የመጠበቂያ ግንብ መጽሐፍ’* የድርጅቱን መሠረተ እምነት “ከአደጋ” ለመጠበቅ እንዲሁም የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ለመቃወም እንዲያስችል ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። መጽሐፉ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነት እንዴት መቃወም እንደሚቻል፥ ኢየሱስ ፍጡር ነው ለሚለው የድርጅቱ ትምህርት “ማስረጃ” የሚያቀርብ፥ መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንዳልሆነ፥ አካላዊ ህልውና እንደሌለው፥ የሥላሴ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑን ይልቁንም ትምህርቱ ከአረማውያን መድበለ አማልክት እንደተወሰደ በተጨማሪም ይህንና ይህን የመሳሰሉ ሌሎች መሠረታዊ የክርስትና አስተምህሮዎችን የሚቃወሙ ርዕሶችን ያካተተ ነው።

ብዙ ክርስቲያኖች ለእንደዚህ ዓይነቱ የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት መልስ ለመስጠት የሚያስችል ዕውቀት የላቸውም። ለዚህም ነው በመናፍቃን ላይ ለብዙ ዓመት የሠራው የሥነ-መለኮት ምሁር፥ ዶክተር ዋልተር ማርቲን “ለአሥራ አምስት ቀናት በይሖዋ ምስክሮች የተማረ ሰው በአሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ የአማካይ [average] ክርስቲያንን እምነት ሊያናጋ ይችላል” የሚለው። ይህ አባባል ለብዙ ዓመት የይሖዋ ምስክሮች ንቁ ተሳታፊ አባል የነበረን የአንድ ሰው ምስክርነት ያስታውሰኛል፡-

> “የይሖዋ ምስክሮች በሚያስተምሩበት ማንኛውም ትምህርት ላይ ‘ማስረጃ’ ይሆናሉ የሚሉአቸውን ጥቅሶች ከእግዚአብሔር ቃል ላይ ይጠቅሳሉ። በዚህም መንገድ ምንም በማያውቀው ለጋ አእምሮዬ ውስጥ *‘የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት’* አስተምህሮን ጠቀጠቁበት። የይሖዋ ምስክር ከመሆኔ በፊት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የማውቀው ነገር አልነበረኝም። በጥቂት ሳምንታት ውስጥ

'ብዙ ስለ አወቅሁ' ለመስክ አገልግሎት ከአስጠኝዬ (ከአስተማሪዬ) ጋር ወጣሁ። በመጀመሪያም ቀን የመስክ አገልግሎቴ ሁለት የባፕቲስት፥ አንድ የሉተራን እንዲሁም ሦስት የፕርስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን አባላትን እምነት አናጋሁ። ብዙ ክርስቲያኖችም ለቃለ እግዚአብሔር መሃይማን የመሆናቸው ጉዳይ እጅግ አስደነቀኝ" [Don Nelson, "That Hideous Strength: The Watchtower Society", Christian Research Newsletter, March/April 1991, p.1]

የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮአቸውን በቃለ እግዚአብሔር ላይ ለማስደገፍ ይረዱናል የሚሉአቸውን ጥቅሶች አጥንተው ነው በራችንን የሚያንኳኩት። ከዚህም በተጨማሪ "ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር" የሚለው 'የመጠበቂያ ግንብ መጽሐፍ' ውስጥ የይሖዋ ምስክሮች ለመስክ አገልግሎት ወጥተው የሚያገኙአቸውን ሰዎች እንዴት መቅረብ እንዳለባቸው፥ ውይይት ቀስቃሽ የሆኑ ርዕሶችን በማቅረብ በመረጡት ርዕስ ጉዳይ ላይ ምን ምን መናገር እንደሚጠበቅባቸው በስፋት ያስተምራል። ይህ ብቻም አይደለም መጽሐፉ፡- "ፍላጎት የለኝም"፥ "ለሃይማኖት ግድ የለኝም"፥ "የይሖዋ ምስክሮችን አልፈልግም"፥ "የራሴ ሃይማኖት አለኝ"፥ "እኛ ክርስቲያኖች ነን"፥ "ሥራ አለብኝ"፥ "አዘውትራችሁ የምትመጡት ለምንድን ነው?"፥ "የእናንተን ሃይማኖት በሚገባ አውቀዋለሁ"፥ "ገንዘብ የለንም"፥ "ቡዲስት ነኝ የሚል ሰው ሲያጋጥም"፥ " 'ሂንዱ ነኝ' የሚል ሰው ሲያጋጥም"፥ " 'አይሁዳዊ ነኝ' የሚል ሰው ሲያጋጥም"፥ " 'እስላም ነኝ' የሚል ሰው ሲያጋጥም" ምን ዓይነት መልስ መስጠት እንዳለባቸው ይተነትናል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተቀናጅቶ የመጣውን የመናፍቃን እንቅስቃሴ ጤናማ በሆነ አስተምህሮ ለመገደብ እንዲያስችል ነው፡- ***"የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን"*** የተባለው ይህ መጽሐፍ የተጻፈው።

ዛሬ በዓለማችን ከ5.5 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት የይሖዋ ምስክሮች በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ ከአንድ ቢሊዮን ሰዓት በላይ በመጠቀም፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ ሳይሆን ፍጡር ነው፤ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና የለውም፥ አምላክም አይደለም ወዘተ የሚለውን አስተምህሮ በየቤቱና በየመንገድ ዳሩ በትጋት ይናገራሉ። ይህንንም ትምህርት በስፋት የሚያትቱትን ጽሑፎች ያሠራጫሉ። በዓለም ዙሪያ በአንድ ደቂቃ 45 ሰኮንድ ውስጥ አንድ ሰው የይሖዋ ምስክር አባል ይሆናል። በእንዲህ ዓይነት ፍጥነት በመስፋፋት ቤተ ክርስቲያንን አሳሳቢ ደረጃ ላይ ያደረሳትን መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ለመግታት እንዲያግዝ ጭምር ነው ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው።

የክርስቶስን ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ የመስበክ ኀላፊነት የተሰጠው ለማን ነው? ዛሬ ለይሖዋ ምስክሮች የምሥራቹን ቃል የሚናገር ማነው? የይሖዋ ምስክሮች ክርስቲያኖችን ጨምሮ በየቀኑ የብዙ ሰዎችን ቤት ያንኳኳሉ፥ ከብዙ ሰዎችም ጋር ይገናኛሉ። ነገር ግን ብዙ ክርስቲያኖች ለይሖዋ ምስክሮች የሚሰጡት መልስ እጅግ አሳዛኝ ነው። እንዲህም በማለት ያባርሩአቸዋል፡- "አዝናለሁ፥ ከእናንተ ጋር ለመወያየት ፈቃደኛ አይደለሁም"፥ "እእእ. . . እናንተ ናችሁ አውቃችኋለሁ"፥ "እኔ ክርስቲያን ነኝ"፥ "ጊዜ የለኝም" ወዘተ። እኛ ክርስቲያኖች ወንጌላውያንን ወይም ሚሲዮናውያንን ራቅ ወዳሉ አገሮች እንልካለን የሚሄዱበትንም አገር ወይም አካባቢ ቋንቋና ባህል እንዲለምዱ አስቸጋሪና ረጅም ጊዜ የሚወስዱ ትምህርቶችንና ሥልጠናዎችን እንሰጣለን። ነገር ግን በራችንን ለሚያንኳኩ፥ ዘውትር በየመንገዱ ዳር ለምናገኛቸው፥ ደኅንነት ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ጊዜና ሸክም እንዴት አጣን? በእርግጥ በመናፍቃን እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉትን ወደ ትክክለኛው መሠረተ እምነት የማምጣት ኀላፊነት አለብን። ለይሖዋ ምስክሮች በክርስቶስ የሚገኘውን የዘላለም ሕይወት ለመናገር ፍላጎቱ እያለን አቀራረቡና ዕውቀቱ ለቸገረን ይህ መጽሐፍ መፍትሔ አለው። መጽሐፉንም ሆነ ትምህርቱን አስመልክቶ ጥያቄ፥ አስተያየትም ሆነ ሂስ ካልዎት በሚከተለው አድራሻ ቢጽፉልኝ ይደርሰኛል፡-

ተስፋ የወንጌላውያን ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር
የመ. ሳ. ቁጥር 70295
አዲስ አበባ

**TESFA Evangelical Society For Apologetics,**
**P. O. Box 70295**
**Addis Ababa, Ethiopia**

ተስፋዬ ሮበሌ
ታኅሣሥ 1991 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# መግቢያና የምልክቶች መፍቻ

ይህ መጽሐፍ አራት ምዕራፎች አሉት። ምዕራፍ አንድና ምዕራፍ አራት ለክርስትና እምነት መናፍቃን ሁሉ ሊያገለግሉ የሚችሉ መሠረታዊ መርሆችን ያካተተ ነው። መቼም ከፀሐይ በታች ያሉትን መናፍቃን ሁሉ እናጥና ብንል ጊዜውም፥ ጉልበቱም ሊኖረን አይችልም። ነገር ግን ዋና ዋና መናፍቃንን [Major Cults] ጊዜ ሰጥተን በማጥናት በተጓዳኝ ደግሞ ሁሉም መናፍቃን ያላቸውን ተመሳሳይ ባሕርይ፥ መናፍቃን ነፍቀዋል የምንለው ከየት ክልል ሲወጡ እንደሆነ፥ ለለ መናፍቃን ማጥናት ያስፈለገበት ምክንያት፥ የመናፍቃን ስኬታማነት ምክንያት ምን እንደሆነ፥ የእግዚአብሔርን መንጋ ከመናፍቃን እንቅስቃሴ እንዴት መጠበቅ እንዳለብን የምንመለከትበት ክፍል ነው።

ምዕራፍ ሁለት የይሖዋ ምስክሮች በዓለም ዙሪያና በኢትዮጵያ ያላቸውን አጠቃላይ እንቅስቃሴና ታሪክ በስፋት የምንማርበት ቦታ ነው።

በምዕራፍ ሦስት በጥልቀት የምንመለከተው የይሖዋ ምስክሮችን አስተምህሮ ነው። ይህ ለአስተምህሮቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ የምንሰጠው በዚሁ ክፍል ነው። ይህ ክፍል በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው። በእያንዳንዱም ክፍል መጀመሪያ ላይ የሚከተሉትን ምልክቶች እናገኛለን፡—



ይህ ምልክት የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር ዓርማ ነው። ይህ ምልክት ባለበት ርዕስ ሥር የምንመለከተው የይሖዋ ምስክሮችን አስተምህሮ የራሳቸውን ጽሑፍ በዋቢነት በማቅረብ ነው።



የመጽሐፍ ቅዱስና የሚዛን ምልክት ባለበት ስፍራ ከላይ የተመለከትነውን የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት በቃለ እግዚአብሔር እንመዝነዋለን።



የመጽሐፍ ቅዱስ ስዕል ባለበት ቦታ መጽሐፍ ቅዱስ በርዕስ ጉዳዩ ላይ የሚያስተምረውን ትምህርት በአጭሩ የምንከልስበት ስፍራ ይሆናል።



በጥያቄ ምልክት ሥር ደግሞ የይሖዋ ምስክሮች ሊጠየቁት የሚገባቸውን ጥያቄዎች አስፍረናል።

የይሖዋ ምስክሮች በእምነታቸው ላይ ሂስ የሚሰነዝሩትን፡— "ተቃዋሚዎች" እንዲሁም እምነቱን ጥለው የወጡትን፡— "አፈንጋጮች" ይሉአቸዋል። ከእነዚህም ሰዎች ጋር መነጋገርም ሆነ ጽሑፎቻቸውን ማንበብ በጥብቅ የተከለከለ ነው። እንዲያውም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት እነዚህን ጽሑፎች፡— "መንፈሳዊ የዝሙት ስዕሎች" ይላቸዋል። "በሰይጣን ጠረጴዛ ላይ ማዕድ መብላት" እንደሆነም አድርጎ ያስተምራል።

በድርጅቱ ትምህርት መሠረት የይሖዋ ምስክሮች ከ"አፈንጋጮች" ወይም ከ"ተቃዋሚዎች" ጎራ ፈርጀውን ከእኛ ጋር ያላቸውን ውይይት እንዳያቆሙ ቁልፍ የሆኑ መሠረታዊ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የአስተምህሮአቸውን ከንቱነትና የድርጅቱን ስህተት ልናሳያቸው እንችላለን።

ጥያቄዎቹ በተለይ ያነጣጠሩት የድርጅቱን ሐሰተኝነት በማጋለጥ ላይ ነው። ምክንያቱም የይሖዋ ምስክሮች የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር ላይ ያላቸው እምነት እጅግ ከፍተኛ ነው። እንደ ይሖዋ ምስክሮች እምነት እግዚአብሔር መንፈሳዊ ምግብ ለሥጋ ለባሽ ሁሉ የሚያወርደው በዚህ ድርጅት አማካኝነት ብቻ ነው። በእግዚአብሔር የሚመራና የእግዚአብሔር ብቸኛ የሆነ ምድራዊ ወኪል ይኸው ድርጅት ነው። እንዲያውም በዚህ ድርጅት ጥላ ሥር ካልተጠለሉ በስተቀር እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ደኅንነት አይሰጥም። የድርጅቱን ጽሑፍ በእማኝነት በማቅረብ የድርጅቱን ሐሰተኝነት ለተከታዮቹ ማሳየት ከብዙ አትጣጫ ጠቀሜታው ታላቅ ነው።

# ማውጫ

## ምዕራፍ አንድ፡- ቅኝት

1.1 ኑፋቄ ማለት ምን ማለት ነው?........................................3
1.2 ስለ መናፍቃን ማጥናት ለምን አስፈለገ?...............................5
1.3 የመናፍቃን ሥነ-መለኮታዊ ባሕርይ...................................7

## ምዕራፍ ሁለት፡- የይሖዋ ምስክሮች አነሣሥና እድገት

2.1 በዓለማችን ላይ ምን ያህል መናፍቃን አሉ?.............................16
2.2 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በዓለም አቀፍ ደረጃ ...................19
2.3 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በኢትዮጵያ..............................21
2.4 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲካዊ ......................................22
ዘገባ በኤርትራና በኢትዮጵያ ..........................................25
2.5 የይሖዋ ምስክሮች ታሪካዊ ዳራ.......................................36
2.6 የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ

## ምዕራፍ ሦስት፡- የይሖው ምስክሮች አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

3.1 የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የአምላክ ድርጅት ነውን?...................50
3.2 የይሖዋ ምስክሮችና የአምላክ ስም ...................................60
3.3 የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮተ ሥላሴ .............................74
3.4 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ......................92
3.5 ደኅንነት በይሖዋ ምስክሮች መንገድ ...............................104
3.6 የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በሞት፥ ..............................123
በነፍስና በሲኦል ላይ................................................132
3.7 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት

## ምዕራፍ አራት፡- ሰዎችን ከመናፍቃን እንዴት እንጠብቅ?

4.1 ሰዎች መናፍቃንን ለምን ይከተላሉ?.................................151
4.2 ሰዎች መናፍቃንን እንዳይከተሉ
እንዴት ልንጠብቃቸው እንችላለን?...................................155
4.3 የይሖዋ ምስክሮችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ..........................160
ተመካሪ አቀራረብ

# ምዕራፍ አንድ

# ቅኝት

1.1 ኑፋቄ ማለት ምን ማለት ነው? ........................3
1.2 ስለ መናፍቃን ማጥናት ለምን አስፈለገ?......5
1.3 የመናፍቃን ሥነ-መለኮታዊ ባሕርይ ..............7

## 1.1 ኑፋቄ ማለት ምን ማለት ነው?

“በአንድ ርዕሰ ነገር ላይ ውይይት ከመጀመራችን በፊት ልናስተላልፈው የምንፈልገውን ሐሳብ በትክክል ሊወክሉልን በሚችሉት ቃላት ላይ ተመሳሳይ እይታ እንዲኖረን በቃሉ ትርጉም እንስማማ።” የሚለውን የጥንት ግሪካውያን አነጋገር በእርግጥ ዘመን የማይሽረው፣ ብልህነት የተሞላበት አባባል ነው። ታዲያ እነዚያ የጥንት ግሪክ ሊቃውንት በዚህ እውነታ ላይ ተንተርሰው በሳይንሱ መስክ ያፈለቋዋቸው ፅንሰሃሳቦች፥ ያደረጓቸው ጥናቶችና ምርምሮች፣ የሰነዘሯቸው መላምቶች፣ ያቀረቡአቸው ንድፈ ሐሳቦች ለዘመናችን ሳይንሳዊ ዕውቀትና ግኝት ፈር ቀዳጅና ፋና ወጊ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። እኛም ኑፋቄ የሚለውን ቃል በመፍታት ትምህርታችንን ብንጀምር ከብዙ አቅጣጫ ጠቀሜታው ታላቅ ነው።

ከቋንቋ አጠቃቀም የምንማረው አብዛኛውን ጊዜ አንድ ቃል ከአንድ በላይ ትርጉም እንዳለው ነው። ነገር ግን የቃሉን አማራጭ ትርጉም የሚወስነው ቃሉ የሚገኝበት ዐረፍተ ነገር ወይም ዐውድ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ኑፋቄ የሚለው ቃል የወከለው ትርጉም ምን እንደሆነ ቀጥለን እንመለከታለን።

### የቃሉ ጥሬ ትርጉም

ከሳቴ ብርሃን ተሰማ፤ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት፤ ኑፋቄ የሚለውን ቃል ከዚህ እንደሚከተለው ይፈታዋል (ገጽ 682)፦

- ነፈቀ – ዐመትን ዕለትን ወርን ከፈለ፥ ለየ፥ ወይም አንድ ሙሉ የኾነ ነገርን ከኹለት ከፈለ፥ ወይም የብርቱካንን፥ የሎሚን አካል ክፍልፍሎች በእየክፍላቸው ለየ። [በዚህ ትርጉም መሠረት ነፈቀ ማለት አንድን ነገር ከሁለት ከፈለ፥ ለየ፥ መደበ ማለት ነው።]

- ነፈቀ – ከሃይማኖት ወጣ፥ ተጠራጠረ፥ መናፈቅን፥ ከሀዲን ኾነ ነፈቀ። [በዚህ ትርጉም መሠረት ነፈቀ ማለት ከትክክለኛው የእምነት መንገድ ወጣ፥ ሳተ ወይም ትክክለኛውን እምነት ካደ፥ ተጠራጠረ ማለት ነው።]

ኪዳነወልድ ክፍሌ፤ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤ ደግሞ ኑፋቄ የሚለውን ቃል እንዲህ ይተረጉመዋል (ገጽ 645–646)

- መናፍቅ (ቃት ቀን) ናፋቂ አናፋቂ፤ የማጠራጠር የሚያጠራጥር፤ ጠርጣሪ አጠራጣሪ፤ ሃይማኖቱ ሕጹጽ የሆነ፥ ሞሉ እና ፍፁም ትክክል ያይደለ፤ መንፈቁን አምኖ መንፈቁን የሚክድ። [በዚህ ትርጉም መሠረት መናፍቅ ማለት እምነቱ ትክክል ያልሆነ፥ ግማሹ እውነት ግማሹ ደግሞ ሐሰት የሆነ እምነት ያለው ማለት ነው።]

- ነፈቀ – መንፈቅ፥ መሠንጠቅ፥ አስተካክሎ መክፈል መለየት። [በዚህ ትርጉም መሠረት ነፈቀ ማለት እኩል ለእኩል ለየ፥ ከፈለ ማለት ነው።]

- ኑፋቄ – በቁሙ፤ መክፈል መካፈል፤ ክፍያ አከፋፈል። ጥርጥር፥ ጥርጠራ፤ ምንታዌ።

ይህ እንግዲህ ነፈቀ ወይም ኑፋቄ ለሚለው የግዕዝ ቃል የቋንቋው ምሁራን ለቃሉ የሰጡት ፍቺ ነው። ይህን ፍቺ መሠረት በማድረግ ነፈቀ፥ ኑፋቄ፥ መናፍቅ የሚሉት ቃላት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የመከሉት ትርጉም ቀጥሎ በጥቅሉ የተባለውን ይመስላል። *መናፍቅ (ነፈቀ/ኑፋቄ) ማለት ትክክለኛውን እምነት የተወ፥ የካደ፥ የጣለ፤ ትክክለኛው እምነት ግማሹን አምኖ ግማሹን የካደ፤ ትክክለኛውን እምነት የሚጠራጠር፥ ልቡና አሳቡ የሚዋዥቅ፥ የሚዋል ማለት ነው።*

## የቃሉ ሥነመለኮታዊ አጠቃቀም

ኑፋቄ ወይም ነፈቀ ለሚለው የግዕዝ ቃል የእንግሊዝኛ አቻ ትርጉሙ ከልት [CULT] እና ሔረሲ [HERESY] የሚሉት ቃላት ናቸው። ከልት የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ከልተስ ከሚል የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም፡– "ለመለኮት አምልኮን አቀረበ ወይም ክብርን ሰጠ" ማለት ነው። የላቲን ቩልጌት ትርጉም ቃሉን የሚጠቀምበት ለእውነተኛው አምላክም ሆነ *ለጣዖታት* የሚቀርበውን አምልኮ በሚያሳይ መልኩ ነው። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 17፥23 የአቴና ሰዎች ያመልኩአቸው ለነበሩት ጣዖታት ይቀርብላቸው የነበረውን አምልኮ ሲያሳይ፤ በቁጥር 25 ላይ ደግሞ "ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ" ለሚሰጠው ልዑል እግዚአብሔር የሚሰጠውን አምልኮና ክብር ለማሳየት ቃሉ ጥቅም ላይ ውሎአል[1]።

1. Alan W. Gomes, Unmasking the Cults. (Grand Rapids: Zondervan, 1995), ገጽ 7



ሔረሲ የሚለው ቃል "ሔረሲስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተወረሰ ሲሆን፤ ትርጉሙም "ምርጫ" ወይም "የተመረጠ ነገር" ማለት ነው። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ግሪክ ሔረሲ የሚለው ቃል በአብዛኛው ጥቅም ላይ የዋለው "ክፍፍል" ወይም ልዩነት በሚለው ትርጉሙ ነው። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን *ሔረሲ የሚለውን ቃል* ትጠቀምበት። የነበረው መሠረታዊ የሆነውን የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እንደሚክድ ትምህርት አድርጋ ነበር (የሐዋ. 24፥14)[2]

በዘመናችን ያሉ ብዙ የሥነ መለኮት ሊቃውንት ኑፋቄ ለሚለው ቃል የሚሰጡት ትርጉም (ግላዬ) የተለያየ ቢሆንም፤ ብዙዎቹ የሚስማሙበት ከዚህ የሚከተለውን ነው፡– *የክርስትና እምነት መናፍቃን እራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ፤ በመሪዎቻቸው ወይም በድርጅቶቻቸው የተሰጠውን የተወሰነ አስተምህሮአዊ ሥርዓት የሚከተሉ፤ ይህም አስተምህሮ ከስልሳ ስድስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን ጽሑፎች የተቀዳውን የክርስትና እምነት መሠረታዊ አስተምህሮ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ትምህርት የሚክዱትን መናፍቃን ብለን እንጠራቸዋለን*[3]። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መናፍቅ የሚለውን ቃል የምንጠቀምበት በሥነ መለኮታዊ አጠቃቀሙ ነው።

## 1.2 ስለ መናፍቃን ማጥናት ለምን አስፈለገ?

መጽሐፍ ቅዱስ ለመናፍቃንና ለትምህርታቸው ትልቅ ትኩረት ሰጥቶአል። የሥነመለኮት ሊቃውንት እንደሚሉት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አንድ ሦስተኛው ያተኮረው በመናፍቃንና በትምህርቶቻቸው ላይ ነው። ይህ እውነታ የሚያስገነዝበን ቅዱሳት መጻሕፍት ለመናፍቃንና ለትምህርታቸው ምን ያህል ትኩረት እንደሰጡና እኛም ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ማጥናት እንዳለብን የሚያስተምረን ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት በርዕስ ጉዳዩ ላይ ሰፊ አስተያየት ሰጥተዋል በማለት ብቻ ፍሬ ነገሩን በደፈናው ማለፍ አግባብ ስለማይሆን በእኛ እምነት ዋና ዋና የምንላቸውን የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ጥቅሶች ከዚህ እንደሚከተለው አቅርበናቸዋል።

- ሐሰተኛ እረኞች፡

ኢሳ. 56፥10–12፤ ኤር. 23፥2፤ 50፥6፤ ሕዝ. 34፥2–3፤ ዮሐ. 10፥12

♦ ሐሰተኛ ነቢያት

ዘዳ. 13፥5፤ 18፥22፤ ኢሳ. 9፥15፤ ኤር. 2፥8፤ 5፥31፤ 14፥14፤ 23፥16፤ ዘካ. 13፥3፤ ሕዝ. 13፥2፤ 22፥28፤ ሆሴ. 9፥7፤ ሚክ. 3፥5፤ ሰፎ. 3፥4፤ ማቴ. 7፥15፤ 24፥11፤ ማር. 13፥22

♦ ሐሰተኛ አስተማሪዎች

ማቴ. 5፥19፤ 15፥9፤ 1ጢሞ. 1፥7፤ 4፥2፤ 6፥3፤ 2ጢሞ. 1፥11፤ 2ጴጥ. 2፥1

ኢየሱስ ክርስቶስ በአገልግሎቱ ዘመን ከሐሰተኛ አስተማሪዎችና እረኞች ጋር በመፋጠጥ ብዙ ጊዜውን አሳልፎአል። በመጨረሻም ለሞት አልፎ የተሰጠው በእነዚህ ሰዎች ነበር።

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል መስበክ ብቻ ሳይሆን ደቀ መዛሙርቱ ሊገጥማቸው ያለውን ውጫዊም ሆነ ውስጣዊ መከራ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። እንደ ጌታ ትምህርት ከእነዚህ መከራዎች ሁሉ እጅግ የከፋው ብዙዎችን በማሳት በእርሱ ስም የሚመጡት የሐሰተኛ ነቢያት፥ እረኞች፥ አስተማሪዎችና የሐሰተኛ ክርስቶሶች ተግዳሮት ነው (ማቴ. 24፥15፤ 7፥15–23)። የመጀመሪያዎቹን አምስት መቶ ዓመታት የሥነ መለኮት ታሪክ ስንመረምር እነዚህ የክርስቶስ ትንቢታዊ ቃሎች እውን ሆነው እናገኛቸዋለን።

ለመገመት በሚያስቸግር ፍጥነት በመስፋፋት ላይ ያለውን የመናፍቃንን ባሕርይ፥ እንቅስቃሴ ጤናማ በሆነ አስተምህሮ ለመግታት የመናፍቃንን ታሪክና አስተምህሮ ጠንቅቀን ማወቅ ይኖርብናል። ምንም እንኳ ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ ሐዋርያት ከመናፍቃንና ከትምህርታቸው እንድንጠነቀቅ ቢያሳስቡንም የኑፋቄ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ መታየቱ አልቀረም። እንዲያውም አሁን በእኛ ዘመን ከክርስትና እምነት ተከታዮች በላይ በጣም እየተስፋፋ ቤተ ክርስቲያንን አሳሳቢ ደረጃ ላይ ያደረሳት የመናፍቃን ከፍተኛ እድገት ነው ("የመናፍቃን ስታቲስቲክ" የሚለውን ክፍል ይመለከቷል)። ለዚህ ነው ቲም ጃኮብሰን የተባሉት የእግዚአብሔር ሰው "ዓለማችን በመሲህ ነን ባዮች መጥለቅለቋ ለማንም ሰው ግልጽ ሆኖ የሚታየው እውነት ነው" ያሉት።

2. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 17
3. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 7



ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የመጠበቅ ኃላፊነቱአን እንድትወጣ እንዲሁም በመናፍቃን እንቅስቃሴ ውስጥ የገቡትን ሰዎች ወደ ትክክለኛው መሠረተ እምነት ለማምጣት የመናፍቃንን ትምህርትና አሠራር ማወቅ ያስፈልጋል። እያንዳንዱ ክርስቲያን ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ የመስበክ ኃላፊነት አለበት። ኃላፊነት ደግሞ አንድ ቀን ያስጠይቃል። ስለዚህ በመናፍቃን ዓለም ውስጥ ያሉትን ሰዎች ቸል ልንላቸው አይገባም። አንዳንድ ክርስቲያኖች የመናፍቃንን መንፈቅ (መሳት) በማወቃቸውና እንቅስቃሴውንም በመኮነን ብቻ ይረካሉ። መናፍቃንን ኮነናቸውም አልኮነናቸው የሚያመጣው ምንም ለውጥ የለም። በመሠረቱ ሰዎችን በመኮነን የሚሠራ ምንም ሥራ የለም። ከዚህ ይልቅ ግን ሰዎች የሚሉትን ነገር በትክክል ተረድቶ ልክ አለመሆናቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ዋቢ አድርጎ በመጥቀስ ማሳየት ያስፈልጋል።

መናፍቃን እንደ ማንኛውም ሰው መዳን ያስፈልጋቸዋል። ምክንያቱም እነርሱ እንደ ሌሎች ሰዎች ጠፍተዋል። ወደ ጠፉ ሰዎች መሄድ ደግሞ የክርስቲያኖች ሁሉ ኃላፊነት ነው። እግዚአብሔር ዐደራ ሰጥቶናል። ያም ዐደራ ለሰዎች ሁሉ እውነተኛውን የምሥራች ቃል መንገር ነው።

## 1.3 የመናፍቃን ሥነመለኮታዊ ባሕርይ[1]

### 1.3.1 "የመናፍቃን ሥነመለኮታዊ ባሕርይ" ስንል ምን ማለታችን ነው?

በዚህ ክፍል የምንመለከተው የመናፍቃንን ሥነ መለኮታዊ ባሕርይ ነው። ይኸውም ከሃይማኖታዊ አስተምህሮአቸው በመጀመር የአስተምህሮአቸውን ከንቱነት እንዴት አድርገን መለየት እንደምንችል በእርጋታ እንመለከታለን። የመናፍቃን ሥነመለኮታዊ አቋም ከልምምዳቸው ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፤ ነገር ግን በዚህ ክፍል ለማየት የምንሞክረው ልምምዳቸውን ሳይሆን ሥነመለኮታዊ አቋማቸውን ነው።

ከዚህ በታች በዝርዝር የምናየው የመናፍቃንን አስተምህሮ ሲሆን ሁሉም መናፍቃን ሁሉንም ባሕርይ ያሳያሉ ማለት ግን አይደለም። ሆኖም አብዛኞቹ መናፍቃን ባሕርያቱን በተወሰነ መጠን ያሳያሉ።

1 ይህ ክፍል በአብዛኛው የተወሰደው፡- Alan W. Gomes. Un masking the Cults. (Grand Rapids: Zondervan, 1995) ገጽ 24–46 በሚል ርዕስ ከጻፈው መጽሐፍ ላይ ነው።

እነዚህ ባሕርያት መሠረታዊ ልዩነት ይፈጥራሉና [ለምሳሌ፡- አስተምህሮተ ሥላሴን መካድ፥ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነት ያለመቀበል ወዘተ]።

አንድ ሰው መናፍቅ የሚባለው ከመሠረታዊው የክርስትና አስተምህሮ ሲያፈነግጥና ይህንንም አስተምህሮ ሲክድ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ከመሠረታዊ እምነታቸው ይልቅ ለልምምዳቸው ትኩረት ይሰጣሉ። እንዲሁም አንዳንድ ክርስቲያናዊ ተቋሞች የተሳሳተ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ዘዴን ይከተላሉ። ይህ አካሄዳቸው መሠረታዊውን የክርስትና ትምህርት እስካልተቃረነ ድረስ ሰዎቹን መናፍቅ ሊያሰኛቸው አይችልም።

## 1.3.2 የመናፍቃን ሥነመለኮታዊ ባሕርይ

### 1. አስተምህሮተ ሥላሴን መካድ

መናፍቃን እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊው የክርስትና አስተምህሮ በአንዱ የእግዚአብሔር ባሕርይ ውስጥ ሦስት ዘላለማዊ አካላት ይኸውም፡- አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እንዳሉ አያምኑም። ምናልባትም ሁሉም መናፍቃን የሥላሴን አስተምህሮ ይክዳሉ ቢባል ከእውነት መራቅ አይሆንም። እንዲያውም አንዳንዶች ለምሳሌ፡- የይሖዋ ምስክሮች የሥላሴን አስተምህሮ ከአረማውያን የመድበል አማልክት አስተሳሰብ ጋር ያመሳስሉታል፤ ይህ አስተምህሮ ከአረማውያን የተቀዳ ነው ብለው በድፍረት ይናገራሉ። አንዳንድ መናፍቃን ደግሞ ሥላሴን እናምናለን ይላሉ። ነገር ግን ሥላሴ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሚያብራሩበት መንገድ ፍጹም የተሳሳተና ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት እጅግ የራቀ ነው።

### 2. ደኅንነት በእምነት አማካይነት በጸጋ መሆኑን ይክዳሉ

ቫን ባለን እንደሚለው የሁሉም መናፍቃን የመጨረሻ ትምህርት ድምዳሜ "ራስህን ማዳን አለብህ"[2] የሚል ነው። ለእግዚአብሔር ጸጋ የከንፈር አገልግሎት ብቻ እንዲሰጡ ያደረጋቸው ክርስቶስ በመስቀል ላይ ያከናወነው የደኅንነት ሥራን ስለሚያቃልሉ ነው። የክርስቶስ የደኅንነት ሥራ በራሱ ሙሉ በሙሉ የማያድን ከሆነ የጎደለውን በሥራ ማካካስ ወይም መሙላት አይቀሬ ነው።

2. J. K. Van Baalen, The Chaos of the Cults (Grand Rapids: Eerdmans, 1962), 359, cited in Alan W. Gomes ገጽ. 26



እንዲያውም አንዳንዶች የክርስቶስ የማዳን ሥራ አንድ ሰው ወደ እምነት ከመምጣቱ በፊት ያለበትን ኃጢአት የማጠብ ኃይል አለው። ነገር ግን ወደ እምነት ከመጣ በኋላ ራሱን ማዳን ያለበት በሥራ እንደሆነ አጠንክረው ያስተምራሉ። ከዚህ በተጨማሪ የክርስቶስ የማዳን ሥራ ትንንሽ ኃጢአቶችን እንጂ ትልልቅ የሚባሉ ኃጢአቶችን እንደማያካትት ይናገራሉ።

ሌሎች ደግሞ የክርስቶስ የደኅንነት ሥራ ለሰው ልጆች ሁሉ እንደሚሆን ነገር ግን እርሱ የጀመረውን እነርሱ ከዳር እንደሚያደርሱት ያውጃሉ።

### 3. የአካል ትንሣኤን ይክዳሉ

የክርስቶስ የአካል ትንሣኤ የክርስትና እምነት ያረፈበት ታሪካዊ መሠረት ነው (1ቆሮ. 15)። መናፍቃን ደግሞ መሠረታዊ የሚባሉ የክርስትናን አስተምህሮ ማጣመም ተቀዳሚ ተግባራቸው ነው። እጅግ የታወቀውና የትንሣኤን አስተምህሮ የሚያጣምመው ትምህርት ትንሣኤን መንፈሳዊ የሚያደርገው ነው። ስለዚህም ክርስቶስ ከሙታን የተነሣው በመንፈስ ነው ይላሉ (ለምሳሌ፡- የይሖዋ ምስክሮች)። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ ትንሣኤ የአካል ለመሆኑ በግልጽ ይናገራል ["የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ" የሚለውን ርዕስ ይመለከቷል] (ሉቃ. 24፥39፤ ዮሐ. 2፥19-21፤ ቆላ. 2:9)

### 4. የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣናዊት ይክዳሉ

አንዳንድ መናፍቃን መጽሐፍ ቅዱስ በስህተት እንደተሞላ ይናገራሉ። አንዳንዶች ደግሞ ሥልጣናዊ ቃልነቱን በመቀነስ "አሮጌው ብርሃን" በማለት ይጠሩታል። ይህም "አዲሱ ብርሃን" ከሚባለው ከእነርሱ አስተምህሮ ማነሱን ያመለክታል።

ሌሎች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል እንደሆነ በመናገሩም መጽሐፍ ቅዱስን ከራሳቸው አስተምህሮ ጋር እንዲስማማ አድርገው "ይተረጉሙታል"። አንዳንዶች የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣናዊነት የሚያቃልሉት ከእነርሱ አስተምህሮ ጋር የሚስማሙ ሌሎች ጽሑፎችን በማዘጋጀት ነው። እነዚህ ጽሑፎች ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ይታያሉ።

## 5. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ መንገድ በመተርጎም አዲስ ትንታኔ ይሰጣሉ

መናፍቃን አብዛኛውን ጊዜ ለክርስቲያናዊ ቃላት አዲስ ትርጓሜ መስጠት ይወዳሉ። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ በ2ቆሮ. 11፥4 ላይ ሐዋርያት ከሰበኩት የተለየ (ገላ. 1፥6–9) ሌላ ክርስቶስ፥ ሌላ መንፈስ፥ ሌላ ወንጌል የሚለውን አጠቃቀም የሚጠቀመው። መናፍቃን ስለ ክርስቶስ፥ ስለ ወንጌል፥ ስለ ደኅንነት አብዝተው ይናገራሉ፤ ነገር ግን ቃሉን የሚጠቀሙበት መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉን በተጠቀመበት መንገድ አይደለም። [ለምሳሌ፡– የይሖዋ ምስክሮች ክርስቶስ ፈጣሪ ነው ይላሉ፤ ነገር ግን እርሱ ራሱ የአብ የመጀመሪያ ፍጥረት ነው። እንግዲህ ክርስቶስ ለይሖዋ ምስክሮች ፈጣሪም ተፈጣሪም ነው ማለት ነው። የመጽሐፍ ቅዱሱ ክርስቶስ ግን፡– ጅማሬ የሌለው፥ ፍጻሜ የሌለው፥ ፍጹም አምላክና በባሕሪው ከአብ ጋር ፍጹም ትክክል የሆነ ነው]። ስለዚህ አንድ መናፍቅ እኔ በክርስቶስ አምናለሁ ቢል፤ ክርስቶስን ምን ብሎ እንደሚያምነው (ፍጹም አምላክ ወይስ ፍጡር) ልንጠይቀው ይገባል። ዋልተር ማርቲን እንደሚለው፡– “ብዙውን ጊዜ ከመናፍቃን ጋር የምናደርገው ውይይት ፍሬ አልባ የሚሆነው ለምንወያይባቸው ጉዳዮች ትክክለኛውን ትርጉም (ግላዊ) ባለመስጠታችንና እነርሱም ምን ማለታቸው እንደሆነ እንዲያብራሩልን ስለማንጠይቃቸው ነው”[3]። ስለዚህ ለመናፍቃን ከመመስከራችን በፊት መናፍቃኑ ቁልፍ የሆኑ ቃላትን እንዴት አድርገው እንደሚጠቀሙባቸው ወይም እንደሚተረጉሙአቸው አስቀድመን ማወቅ ምስክርነታችንንም ሆነ ውይይታችንን ፍሬያማ እንዲሆን ያደርገዋል።[4]

## 6. ድርጅቶቻቸውና መሪዎቻቸው የእግዚአብሔር ብቸኛ እንደራሴዎች እንደሆኑ ይናገራሉ

የብዙ መናፍቃን መሪዎች የእግዚአብሔር ብቻኛ ወኪሎች፥ ድርጅታቸውም በአምላክ የሚመራ ፍጹም ብቸኛ ድርጅት፥ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝባቸው መንገዶች፥ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ መገለጥ ተቀባዮች አድርገው ራሳቸውን ያቀርባሉ።

3. Martin. Kingdom of the Cults. ገጽ 19. Cited in Alan W. Gomes. ገጽ .31
4. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 24



በዚህ ጉዳይ ላይ እንደ አብነት ሊጠቀሱ የሚገባቸው የይሖዋ ምስክሮች ናቸው። “የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር” [The Watchtower Bible and Tract Society] በመባል የሚታወቀው ድርጅታቸው የአምላክ ፍጹም ብቸኛ ድርጅት እንደሆነ ይናገራሉ። የድርጅቱም ሥልጣናዊ መዋቅር “ታማኝና ልባም በሆኑ ባሪያዎች” እንደተሞላ፥ እነዚህም ባሪያዎች ወቅታዊ የሆነውን መንፈሳዊ ምግብ በወቅቱ እንደሚያወርዱ የእግዚአብሔር እንደራሲዎች[5] ይታያሉ።

## 7. ከአስተምህሮአቸው ጋር የሚቃረኑ ትምህርቶችን ዘለው ያልፋሉ [Compartmentalization]

በርካታ መናፍቃን ከአዋጃቸው ጋር የሚቃረኑ እውነታዎችን ትኩረት አይሰጡአቸውም ወይም አቃለው ይመለከቱአቸዋል። ለምሳሌ፡– የይሖዋ ምስክሮች ብዙ እውነት ሲሆኑ ያልታዩ የሐሰት ትንቢቶችን ተንብየዋል፤ ነገር ግን ይህንን አስተምህሮ እንዲገነቡ ያደረጋቸውን ትንቢታዊ መጽሐፍትን አተረጓጎም ዘዴ አሁንም አልቀየሩም። የአርማጌዶን ጦርነት በ1914 ዓ.ም. ይሆናል ተብሎ ነበር በዚህ ወቅት ሊሆን ሳይችል ሲቀር ቀኑ ወደ 1915 ዓ.ም. ከዚያም 1975 እና 1981 ተሸጋገረ[6]። ነገር ግን ይህን ትንቢት የተናገረው ድርጅት አሁንም ራሱን ከአምላክ ትንቢታዊ እውነት ተቀባይ አድርጎ ይቆጥራል።

## 8. የዘላለምን ቅጣት ይክዳሉ

ብዙ መናፍቃን የእግዚአብሔር ቃል ስለ ዘላለም ቅጣት የሚያስተምረውን ትምህርት አይቀበሉም። አንዳንዶች ለምሳሌ የሁለንታዊ [Universalism] ትምህርት አራማጆች የሰው ልጆች ሁሉ የዘላለምን ሕይወት እንደሚያገኙ ሲያስተምሩ፤ ሌሎች ደግሞ አምላክ ኃጢአተኞችን ወደ አለመኖር [Annihilation] ደረጃ ያመጣቸዋል እንጂ ለዘላለም በገሃነም አይቀጣቸውም የሚል እምነት አላቸው። ለምሳሌ ጆሴፍ ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ[7] በድፍረት “የዚህ [የዘላለም ቅጣት] እግዚአብሔርን የማያከብር አስተምህሮ ጠንሳሽ ሰይጣን ነው። ይህንንም ያደረገበት ምክንያት ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዳያነቡ ለማስፈራራትና እግዚአብሔርን እንዲጠሉ ለማድረግ ነው”[8] ብሎአል።

5. በምድር በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ (1991)። ገጽ 191–195 እንዲሁም፡– ከቅዱሳን ጽሑፎች [illegible] ማመራመር (1994) ገጽ 280–283
6. The Watchtower (1 April 1972).
7. የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ሁለተኛ ፕሬዝዳንት የነበረ ነው።
8. Rutherford, Let God Be True. ገጽ 79 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።

## 9. ከአስተምህሮአቸው ይልቅ ለልምምዳቸው ትኩረት ይሰጣሉ

አንዳንድ መናፍቃን ከእውነት ይልቅ ለስሜት ከፍተኛ ቦታ ይሰጣሉ። በዚህ መሰሉ የመናፍቃን እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉ ሰዎች አስተምህሮአችን ከእግዚአብሔር ቃል የመነጨ ነው ወይ? ለሚለው ጥያቄ ሳይሆን ጥሩ ስሜት ተሰምቶኛል ወይ? ከቀድሞው ልምምዴ ጋር ይስማማል ወይ? ለሚለው ትኩረት ይሰጣሉ። ስሜትና የግል ልምምድ መጥፎ ነው ለማለት አይደለም። ነገር ግን ስሜትም ሆነ ልምምድ ተገቢ የሆነውን ስፍራ መያዝ አለባቸው። የእግዚአብሔር ቃል "እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህ፥ በፍጹም ሐሳብህ [Mind] ውደድ" ይላል (ዘዳ. 6፥5፤ ማቴ. 22፥37፤ ማር. 12፥30፤ ሉቃ. 10፥27)። ይህም ዓይነቱ አምልኮ እውነትን ከስሜት ጋር አጣምሮ የያዘ ነው። እንዲህ ቢባልም የክርስቲያኖች እምነት በእውነታ ላይ የተመሠረተ መሆኑን መዘንጋት አይገባም። በእርግጥ እውነት እንደፈረሰ፥ ስሜት ደግሞ እንደጋሪ ተከታትለው ሊሄዱ ይገባል።

## 10. ከእግዚአብሔር በቀጥታ ተቀበልናቸው ለሚሉአቸው መገለጦችና ራእዮች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ

መናፍቃን በተለይም የእንቅስቃሴው መሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር ካላቸው ቀጥተኛ ግንኙነት የተነሣ ራእይ እና መገለጥ እንደሚወርድላቸውና እግዚአብሔርም ለሕዝቡ የሚሆነውን መንፈሳዊ ምግብ የሚሰጠው በእነርሱ በኩል ብቻ እንደሆነ ይናገራሉ። አብዛኛውን ጊዜ መገለጦቻቸውና ራእዮቻቸው የሚያተኩሩት የመጨረሻውን ዘመን በተመለከተ ሲሆን በዚያን ጊዜ የእነርሱ ዕጣ ፈንታ ምን እንደሆነ የሚናገሩ ናቸው። ቃል እግዚአብሔር "ሁሉንም መርምሩ መልካሙን ያዙ" (1ተሰ. 5፥21) ይለናል ትንቢቱ እንደተነገረው ካልተፈጸመ ትንቢቱም ሆነ ነቢዩ ከእግዚአብሔር አይደሉም ማለት ነው (ዘዳ. 18፥22)። የአንድ ትንቢት ትክክለኛነት የሚረጋገጠው ትንቢቱ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በመስማማቱ ነው (ኢሳ. 8፥20)።

## 11. ለተአምራቶችና ለምልክቶች ከፍተኛ ስፍራ ይሰጣሉ

እግዚአብሔር በእውነተኛ ክርስቲያኖች በኩል ድንቅና ተአምር ሊያደርግ ይችላል። ነገር ግን መሠረታዊውን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ የሚክዱ ሰዎች ድንቅና ተአምር ሊያደርጉ አይችሉም (ዘዳ.



18፥22፤ ኢሳ. 8፥20)። እነዚህ ሰዎች ተአምራትን ካደረጉ ያደረጉት ተአምራት ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከሰይጣን ነው (2ተሰ. 2፥9)።

## 12. ሥነፍጻሜን በተመለከተ የጊዜ ሰሌዳ አላቸው

ብዙ መናፍቃን ሥነፍጻሜን በተመለከተ ቋሚ የጊዜ ሰሌዳ አላቸው። ያስቀመጡትንም ቀን የእግዚአብሔር ቃል እንዲደግፍላቸው የተሳሳተ የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ዘዴን ይጠቀማሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥነፍጻሜ የሚሰጠውን ትምህርት ማወቅ ለዚህ ጊዜ ይጠቅማል። በተለይ የክርስቶስን አዳኝነት ለማይቀበሉ የፍርድ ቀን እንደሚመጣ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ማቴ. 25፥31-46፤ ዕብ. 9፥27፤ ራእ. 20፥12-15)። የወቅቱን ሁኔታ ተመልክቶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንተና ለመስጠት መሞከር ጨርሶ ትክክል አይደለም። ለምሳሌ፦ በባሕር ሰላጤው ጦርነት ጊዜ ፕሬዝዳንት ሳዳም ሁሴንን እንደ ክርስቶስ ተቃዋሚ (Antichrist) ሁኔታውን ደግሞ እንደ ዓለም መጨረሻ አድርገው ያስተማሩ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለመፍታት የሞከሩት ከወቅቱ ሁኔታ ተነሥተው በመሆኑ ወደ ተሳሳተ መደምደሚያ ደርሰዋል። ለዚህ ሁሉ ያበቃቸው መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጎምና ለመፍታት የተጠቀሙበት ስልት ነው።

## 13. የአማኞችን የክህነት አገልግሎት ይክዳሉ

መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች ሁሉ ካህናት እንደሆኑ ያስተምራል (1ጴጥ. 2፥4-10፤ ራእ. 1፥6፤ 5፥10)። ይህም ማለት እያንዳንዱ አማኝ በቀጥታ ከጌታ ጋር መገናኘት ይችላል ማለት ነው።

የበርካታ መናፍቃን መሪዎች፥ ተከታዮቻቸው ለድርጅቶቻቸውና ለትምህርቶቻቸው እንዲገዙ ለማድረግ የአማኞች የክህነት አገልግሎት ይክዳሉ (1ዮሐ. 2፥26-27)።

## 14. ትክክለኛ የሆነውን የቅዱሳት መጽሐፍት አፈታት መንገድ አይከተሉም

መናፍቃን ትምህርታቸን ልክ ነው ለማለት የሚሞክሩት የተሳሳተ የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ዘዴን በመጠቀም ነው። ይኸውም አንድን ጥቅስ ወይም ቃል ከዐውደ ንባቡ አላቀው ይተረጉሙታል። ለሰዋሰው አወቃቀሩም ሆነ ለክፍሉ ታሪካዊ ዳራ እንዲሁም ለክፍሉ ሥነ

ጽሑፋዊ ቅርጽ ቦታ አይሰጡም። አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች ራሳቸው የተሳሳተ የቅዱሳት መጻሕፍት አፈታት ዘዴን የሚጠቀሙበት ወቅት አለ። ድርጊቱ የሚወገዝ ቢሆንም እንኳ ይህ አጠቃቀማቸው ከመሠረታዊው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር እስካልተጋጨ ድረስ መናፍቃን ልንላቸው አንችልም።

### 15. ለደቃቅ አስተምህሮዎች ከፍተኛ ቦታ ይሰጣሉ

ብዙ መናፍቃን ለመሠረታዊው አስተምህሮ ከሚሰጡት ስፍራ ይልቅ ለትናንሽ ትምህርቶች የሚሰጡት ስፍራ እጅግ ከፍ ያለ ነው። ለምሳሌ፡- ለአለባበስ፥ ለአምልኮ ቀናት፥ ለክብረ በዓላትና፥ ለልደት ቀናት ወዘተ የሚሰጡት ቦታ እጅግ የላቀ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

# የይሖዋ ምስክሮች አነሣሥና እድገት


2.1 በዓለማችን ላይ ምን ያህል መናፍቃን አሉ? ........... 16
2.2 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በዓለም አቀፍ ደረጃ ..... 19
2.3 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በኢትዮጵያ ............ 21
2.4 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲካዊ ዘገባ በኤርትራና በኢትዮጵያ .................................. 22
2.5 የይሖዋ ምስክሮች ታሪካዊ ዳራ ................................ 25
2.6 የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ ........................................ 36

## 2.1 በዓለማችን ላይ ምን ያህል መናፍቃን አሉ?

ይህን ጥያቄ በትክክል ለመመለስ አዳጋች የሚያደርጉት በርካታ ምክንያቶች አሉ። አንደኛው ምክንያት ትክክለኛ ስታቲስቲካዊ ዘገባ አለማግኘት ነው። በጉዳዩ ላይ ሰፊ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንደሚያስገነዝቡን በአሁኑ ወቅት ወደ 30 ሚሊዮን የሚደርሱ መናፍቃን በዓለማችን ይገኛሉ። የመናፍቃኑ ብዛት ምን ያህል እንደሆነ በትክክል እንዳይታወቅ ያደረገው ምክንያት ድርጅቶቹ የተከታዮቻቸውን ቁጥር በትክክል አለማወቃቸው ነው። ሁለተኛው ምክንያት የሥነ መለኮት ምሁራን "ኑፋቄ" ለሚለው ቃል የሚሰጡት ግላዊ አንድ ወጥ አለመሆኑና ይህ ቃል እነማንን በቃሉ ትርጉም ሥር እንደሚያካትት ከአንድ ተመሳሳይ አቋም ላይ አለመደረሱ ነው። ለማንኛውም በተለያዩ አጋጣሚዎች ይፋ የሆኑ ስታቲስቲካዊ ዘገባዎችን መሠረት በማድረግ የመናፍቃኑ ብዛት ምን ያህል እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል። አሁን የይሖዋ ምስክሮችን አጠቃላይ ስታቲስቲክ ወደ መመልከቱ እንዝለቅ።

### በዓለማችን ላይ ምን ያህል የይሖዋ ምስክሮች አሉ?

### 1. የአባላት ብዛት

እንደ ጎርጎርዮሳውያን የዘመን አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. በ232 አገሮች በተደረገው ቆጠራ ንቁ የይሖዋ ምስክር ተሳታፊ አባላት ቁጥር 5,599.931 ሲሆን ይህ ቁጥር በ1998 ዓ.ም. ወደ 6 ሚሊዮን ያሻቅባል ተብሎ ይገመታል። በ1997 ዓ.ም. በተደረገው የ"መታሰቢያ" አገልግሎት ["Memorial" Service] (የይሖዋ ምስክሮች የጌታን እራት የሚያስቡበት ቀን የመታሰቢያ አገልግሎት ብለው ይጠሩታል) 14,322,226 ሰዎች ፕሮግራሙን ተካፍለዋል[1]። ይህ የሚያሳየን የይሖዋ ምስክሮች ከንቁ ተሳታፊ አባሎቻቸው እጥፍ በላይ በሆኑ ሰዎች ላይ አወንታዊ ተጋቦት እንዳላቸው የሚያመላክት ነው። በዓለም ዙሪያ በአንድ ደቂቃ 45 ሴኮንድ ውስጥ አንድ ሰው የይሖዋ ምስክር አባል ይሆናል[2]። በዓለማችን 73,070 የይሖዋ ምስክር ጉባዔዎች ይገኛሉ[3]። (የይሖዋ ምስክሮች ስብሰባቸውን "ጉባዔ" ብለው ይጠሩታል)።

---

1. "1998 Year bookook of Jehovah's Witnesses", ገጽ.31
2. Alan W. Gomes, Unmasking the Cults. ገጽ.22
3. ዝኒ ከማሁ።



### 2. የእድገት መጠን

የይሖዋ ምስክሮች የእድገት ፍጥነት እጅግ አስደንጋጭ ነው። በ1965 ዓ.ም. 1.1 ሚሊዮን የነበረው ንቁ ተሳታፊ ሕባላት ቁጥር በ1980 ዓ.ም. ወደ 2.2 ሚሊዮን፤ በ1992 ደግሞ ወደ 4.4 ሚሊዮን አሻቅቦአል። በ1994 ዓ.ም.፥ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ፥ በሶቭየት ኅብረት ብቻ 27,000 ሰዎችን አጥምቀዋል[4]። በዓለም ዙሪያ በየዓመቱ 50 አዳዲስ ጉባዔዎች ይቋቋማሉ[5]።

### 3. ሚስዮናዊ እንቅስቃሴ

የይሖዋ ምስክሮች በ1997 ዓ.ም. ብቻ ለመስክ ምስክርነት 1,179,735,841 ሰዓታትን ተጠቅመዋል[6]። ይህን ቁጥር ለንቁ ተሳታፊ አባሎቻቸው ቁጥር ስናካፍለው እያንዳንዱ አባል ለመስክ ምስክርነት በዓመት ከ200 ሰዓታት በላይ ተጠቅሞአል ማለት ነው። በ1997 ዓ.ም. የተከታዮቻቸውን ልጆች ቁጥር ጨምሮ 375,923 ሰዎችን አጥምቀዋል[7]። ይህ የሚያሳየን የይሖዋ ምስክሮች ለአንድ ሰው በአማካኝ 3,500 ሰዓታትን መጠቀማቸውን ነው[8]። አንድ ንቁ የይሖዋ ምስክር ተሳታፊ አባል በአማካይ በአንድ ወር 18 ሰዓታትን ለመስክ ምስክርነት ያውላል[9]። በ1970 ዓ.ም. አንድ ንቁ አባል በዓመት ለመስክ አገልግሎት ("የመስክ አገልግሎት" የሚባለው በየመንገድ ዳሩና በየቤቱ የመጠበቂያ ግንብ ወንጌልና ጽሑፎችን ማሠራጨት ነው) 150 ሰዓታትን ያውል የነበረ ሲሆን በ1992 ዓ.ም. ይህን ሰዓት በማሻሻል አንድ አባል በዓመት 236 ሰዓታትን በመስክ ምስክርነት ላይ ያሳልፋል[10]።

---

4. Christian Reasearch Institute, "Cult Growth Statistics," citing the watchtower (1 January 1993):ገጽ 15,26.
5. ዝኒ ከማሁ። the Watchtower Society Video, Jehovah's Witnesses: the Organization Behind the maire (1990) ጠቅሶ እንደጻፈው።
6. "1998 Yearbook of Jehovah's Witnesses" ገጽ.31
7. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 31
8. Robert M. Bowman, Jr. Jehovah's Withnesses. (Grand Rapids: Zon., 1995) ገጽ.14
9. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 15
10. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 16

## 4. የጽሑፍ ሥርጭትና የመገናኛ ብዙሃን

ከማንኛውም መናፍቃን ይልቅ የጽሑፍ ውጤቶችን በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቀሙት የይሖዋ ምስክሮች ናቸው። የይሖዋ ምስክሮች በዓለም ዙሪያ 33 ታላላቅ ማተሚያ ቤቶች አሏቸው። “ቤቴል” በመባል የሚታወቀው ትልቁ ማተሚያ ቤታቸው ብቻ በቀን ርዝመቱ 1,000 ማይል (1, 609 ኪሎ ሜትር) የሚያህል ወረቀት ወይም 61 ሚሊዮን ገጽ ወረቀት ያትማል[11]። ከዚህ በተጨማሪ በወር 3ሚሊዮን የአዲሲቱን ዓለም ትርጉም (የይሖዋ ምስክሮች “የአዲሲቱን ዓለም ትርጉም” ከመጀመሪያው ቅጂ ላይ የተተረጎመ ነው ቢሉም ትርጉሙ ግን ከትምህርታቸው ጋር እንዲስማማ ተደርጎ የተሠራ መጽሐፍ ነው) እያተመ ያወጣል። በ1991 ዓ.ም. በእነዚህ ማተሚያ ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ 11,000 የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች ነበሩ[12]።

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ጽሑፎቹን በ210 ቋንቋዎች ይተረጎማል። “መጠበቂያ ግንብ” በሚል ርዕስ የሚታተመው መጽሔት በብዛት ከሚታተሙት መጽሔቶች ውስጥ ዋንኛው ነው፤ መጽሔቱ በወር ሁለት ጊዜ የሚታተም ሲሆን በእያንዳንዱ እትም 16 ሚሊዮን ቅጂዎች ይባዛሉ፤ በ120 ቋንቋዎችም ይተረጎማሉ። አሥራ አምስት ሚሊዮን የሚያህለው ቅጂ የሚታተመው በእንግሊዝኛ ነው። ሥርጭቱም ሪደርስ ዳጀስትና ቲቪ ጋይድ ከሚባሉት መጽሔቶች ካላቸው ሥርጭት ጋር የሚስተካከልና፤ ሽያጩም ከታይምስ፥ ከኒውስዊክ፥ ከዮኤስ ኒውስና፥ ከወርልድ ሪፖርት ጋር ይወዳደራል[13]። “ንቁ” በመባል የሚታወቀው የድርጅቱ መጽሔት በ13 ሚሊዮን ቅጂዎች ሲባዛ በ75 ቋንቋዎች ይተረጎማል[14]።

የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም በ1990 ዓ.ም. ብቻ በ67 ሚሊዮን ቅጂዎች የተባዛ ሲሆን በ14 ቋንቋዎች ተባዝቶ ለንባብ በቅቶአል። በአሁኑ ጊዜ ይህ መጽሐፍ ከ16 በሚበልጡ ቋንቋዎች ተተርጉሞአል[15]።

“ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራው እውነት” በሚለው ስያሜ ተጽፎ የታተመው መጽሐፍ በ1968 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ሲታተም በሥርጭት ደረጃ ቀዳሚውን ስፍራ ከያዙት አምስት መጻሕፍት መካከል አንዱ ሊሆን በቅቶአል[16]።

11. CRI “Cult Growth Statistics”, citing the watchtower (1 Jan. 1993): 19 b
12. David A. Reed, Jehovah's Withness Literature: a Critical Guide to Watchtower Publications (Grand Rapids: Baker, 1993) ገጽ. 9
13. Alan W.Gomes, Unmasking the Cults, ገጽ. 23
14. Robert M. Bowman, Jr. Jehovah's Witnesses, ገጽ. 15
15. Alan W. Gomes, Unmasking the Cults, ገጽ.23
16. Bowman, ገጽ. 15



### 2.2 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በዓለም አቀፍ ደረጃ አጠቃላይ እንቅስቃሴ[1] ከ1991–1997[2] ዓ.ም. ድርጅቱ የሚንቀሳቀስባቸው አገሮች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 211 | 229 | 231 | 232 | 232 | 233 | 232 |

የጉባዔዎች ብዛት

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 66,207 | 69,558 | 73,070 | 75,573 | 78,620 | 81, 908 | 85,256 |

በመታሰቢያ ቀን የተገኙ ሰዎች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 10,650,158 | 11,431,171 | 11,865,765 | 12,288,917 | 13,147,201 | 12,921,933 | 14,322,226 |

የመታሰቢያ ቀን ተካፋዮች[3]

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 8,850 | 8,683 | 8,693 | 8,617 | 8,645 | 8,757 | 8,795 |

በመንግሥት አገልግሎት የተገኙ ንቁ ተሳታፊ አባላት

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 4,278,820 | 4,289,737 | 4,709,889 | 4,914,094 | 5,199,895 | 5,413,769 | 5,599,931 |

1. የግርጌ ማስታወሻ ካልተደረገበት በስተቀር መረጃዎቹ ሁሉ የተገኙት “Yearbook of Jehovah's Witnesses” በሚል ስም ድርጅቱ በየዓመቱ እያሳተ ከሚያወጣው መጽሐፍ ላይ ነው።
2. የዘመን አቆጣጥሩ እ. ኢት. አ. ካልተባለ በቀር በጎርጎርዮሳውያን መሠረት ነው።
3. ኅብስቱንና ጽዋውን የወሰዱ የመቶ አርባ አራት ሺው አካላት (“ቅቡዓን”)

### በመስክ ምስክርነት በየወሩ የሚካፈሉ

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 4,071,954 | 4,289,737 | 4,483,900 | 4,695,111 | 4,950,334 | 5,413,769 | 5,335,078 |

### የእድገት መጠን በመቶኛ

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 5.9 | 5.3 | 4.5 | 5 | 5 | 4.4 | 3.6 |

### የየዓመቱ ተጠማቂያን

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 300,945 | 301,002 | 296,004 | 314,818 | 338,491 | 366,579 | 375,923 |

### ለመስክ አገልግሎት የዋለው ሰዓት

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 951,870,021 | 1,278,127,000 | 1,057,341,972 | 1,096,065,354 | 1,150,353,44 | 1,140,621,714 | 1,179,735,841 |

### በየወሩ በቤት ውስጥ የተደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 3,947,261 | 4,278,127 | 4,515,587 | 4,701,357 | 4,865,060 | 8,855,030 | 4,552,589 |

### ለልዩ አቅኚዎች፥ ለሚሲዮናውያን ክፍያ እንዲሁም ለመስክ አገልግሎት የመጓጓዣ ወጪ በዶላር

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 40,219,589.01 | 45,218,257.59 | 48,857,112.38 | 50,126,004.05 | 57,955,025.64 | 60,932,324.26 | 63,914,602.00 |

### ዋና ቢሮዎች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 97 | 98 | 100 | 100 | 101 | 104 | 104 |



## 2.3 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በኢትዮጵያ[1] ከ1991–1997[2] ዓ.ም.

### ንቁ ተሳታፊ አባላት

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 3,020 | 3,887 | 3,884 | 4,446 | 4,895 | 5,206 | 5,649 |

### ንጥጥር፤ አንድ የይሖዋ ምስክር ለ__________ሰው

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 16,391 | 13,121 | 12,358 | 12,371 | 11,236 | 10,565 | 9,736 |

### ለመስክ አገልግሎት የሚወጡ አስፋፊዎች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 2,730 | 3,533 | 3,525 | 4,144 | 4,626 | 5,036 | 5,292 |

### የእድገት መጠን በመቶኛ

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 13 | 29 | 19 | 18 | 12 | 9 | 5 |

### የየዓመቱ ተጠማቂያን

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 502 | 665 | 449 | 794 | 619 | 581 | 548 |

### የአቅኚዎች ቁጥር[3] (ave. Pio. Pubs.)

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 483 | 770 | 799 | 983 | 1,113 | 985 | 916 |

---

1 የግርጌ ማስታወሻ ካልተደረገበት በስተቀር መረጃዎቹ ሁሉ የተገኙት “Yearbook of Jehovah’s Witnesses” በሚል ስም ድርጅቱ በየዓመቱ እያሳተመ ከሚያወጣው መጽሐፍ ላይ ነው።

2 የዘመን አቆጣጠሩ እ. ኢት. አ. ካልተባለ በቀር በጎርጎርድሳውያን መሠረት ነው።

3 አቅኚ የሚባሉት የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች ናቸው።

### የጉባዔዎች ብዛት

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 54 | 54 | 48 | 48 | 72 | 76 | 79 |

### ለመስክ አገልግሎት የዋለው ሰዓት

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 862,403 | 1,269,513 | 1,289,350 | 1,550,349 | 1,688,752 | 1,654,474 | 1,570,141 |

### በቤት ውስጥ የተደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 3,726 | 4,778 | 4,677 | 4,834 | 4,866 | 4,402 | 3,674 |

### በመታሰቢያ ቀን የተገኙ ሰዎች

| ዓ. ም. | 1991 | 1992 | 1993 | 1994 | 1995 | 1996 | 1997 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 7,192 | 10,980 | 11,932 | 13,246 | 13,742 | 14,677 | 15,716 |

## 2.4 የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲካዊ ዘገባ
## በኤርትራና በኢትዮጵያ[1]
## ከ1951–1990[2] ዓ.ም.
## ንቁ ተሳታሪ አባላት

| ዓ. ም. | 1951 | 1952 | 1953 | 1954 | 1955 | 1956 | 1957 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 18 | 32 | 51 | 67 | 81 | 103 | 119 |

| ዓ. ም. | 1958 | 1959 | 1960 | 1961-1966 | 1967 | 1968 | 1969 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 128 | 109 | 105 | ምንም ዓይነት አሀዛዊ መረጃ አልወጣም | 253 | 313 | 384 |

1. የግርጌ ማስታወሻ ካልተደረገበት በስተቀር መረጃዎቹ ሁሉ የተገኙት "Yearbook of Jehovah's Witnesses" በሚል ስም ድርጅቱ በየዓመቱ እያሳተመ ከሚያወጣው መጽሐፍ ላይ ነው።
2. የዘመን አቆጣጠሩ እ. ኢት. አ. ካልተባለ በቀር በጎርጎርዮሳውያን መሠረት ነው።



| ዓ. ም. | 1970 | 1971 | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 | 1976 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 498 | 596 | 829 | 931 | 1,844 | 1,637 | 1,903 |

| ዓ. ም. | 1977 | 1978 | 1979 | 1980[3] | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 1,824 | 1,593 | 1,475 | 596 | ምንም ዓይነት አሀዛዊ መረጃ አልወጣም | 2,413 |

### ንቁ ተሳታፊ አባላት በአማካይ

| ዓ. ም. | 1951 | 1952 | 1953 | 1954 | 1955 | 1956 | 1957 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | | 21 | 40 | 57 | 63 | 80 | 104 |

| ዓ. ም. | 1958 | 1959 | 1960 | 1961-1966 | 1967 | 1968 | 1969 | 1970 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 117 | 104 | 89 | ምንም ዓይነት አሀዛዊ መረጃ አልወጣም | | 275 | 275 | 437 |

| ዓ. ም. | 1971 | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 | 1976 | 1977 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 528 | 711 | 860 | 1,185 | 1,537 | 1,809 | 1,811 |

| ዓ. ም. | 1978 | 1979 | 1980 | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 1,466 | 1,180 | | ምንም ዓይነት አሀዛዊ መረጃ አልወጣም | 2,413 |

### የየዓመቱ ተጠማቂያን

| ዓ. ም. | 1969 | 1970 | 1971 | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 19 | 142 | 50 | 269 | 322 | 368 | 370 |

| ዓ. ም. | 1976 | 1977 | 1978 | 1979 | 1980 | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 350 | 85 | 84 | 44 | | ምንም ዓይነት አሀዛዊ መረጃ አልወጣም | |

### አቅኚዎች

| ዓ. ም. | 1951 | 1952 | 1953 | 1954 | 1955 | 1956 | 1957 | 1958 | 1959 | 1960 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | | | 13 | 10 | 11 | 14 | 19 | 12 | 10 | 3 |

3. 1981 መረጃ የተገኘው ከ Barrett 1982, 286. ላይ ነው።

| ዓ. ም. | 1961-1966 | 1967 | 1968 | 1969 | 1970 | 1971 | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | ምንም ዓይነት አህዛዊ መረጃ አልወጣም | | 5 | 9 | 18 | 42 | 58 | 65 | 101 | 155 |

| ዓ. ም. | 1976 | 1977 | 1978 | 1979 | 1980 | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 144 | 136 | 101 | 8 | | ምንም ዓይነት አህዛዊ መረጃ አልወጣም | |

### የጉባዔዎች ብዛት

| ዓ. ም. | 1951 | 1952 | 1953 | 1954 | 1955 | 1956 | 1957 | 1958 | 1959 | 1960 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | | | 4 | 5 | 5 | 6 | 7 | 8 | 10 | 10 |

| ዓ. ም. | 1961-1966 | 1967 | 1968 | 1969 | 1970 | 1971 | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | ምንም ዓይነት አህዛዊ መረጃ አልወጣም | | 4 | 4 | 6 | 8 | 10 | 14 | 26 | 44 |

| ዓ. ም. | 1976 | 1977 | 1978 | 1979 | 1980 | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 49 | 50 | 50 | 41 | 8 | ምንም ዓይነት አህዛዊ መረጃ አልወጣም | |

### በቤት ውስጥ የተደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች

| ዓ. ም. | 1951 | 1952 | 1953 | 1954 | 1955 | 1956 | 1957 | 1958 | 1959 | 1960 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | | | 107 | 130 | 140 | 192 | 263 | 271 | 118 | 123 |

| ዓ. ም. | 1961-1966 | 1967 | 1968 | 1969 | 1970 | 1971 | 1972 | 1973 | 1974 | 1975 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | ምንም ዓይነት አህዛዊ መረጃ አልወጣም | | 509 | 2,309 | 800 | 989 | 1,105 | 1,159 | 1,607 | 2,309 |

| ዓ. ም. | 1976 | 1977 | 1978 | 1979 | 1980 | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 2,719 | 2,174 | 4,316 | 1,076 | | ምንም ዓይነት አህዛዊ መረጃ አልወጣም | |


### በመታሰቢያ ቀን የተገኙ ሰዎች

| ዓ. ም. | 1976 | 1977 | 1978 | 1979 | 1980 | 1981-1989 | 1990 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 4,732 | 4,974 | 4,316 | 3,815 | | ምንም ዓይነት አህዛዊ መረጃ አልወጣም | |



## 2.5 የይሖዋ ምስክሮች ታሪካዊ ዳራ[1]

የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ ከመሥራቾቹና ከመሪዎቹ ታሪክ ጋር የተቆራኘ ስለሆነ የእነዚህን ግለሰቦች ታሪክ ማጥናት የድርጅቱን ታሪካዊና ሥነ-መለኮታዊ መሠረት አጥርቶ ለማየት ይረዳል።



"መጋቢ" ችርልስ ታዝ ራስል (1852–1916)

"መጋቢ" ቻርልስ ታዝ ራስል በቀድሞ አልገኒ አሁን የፒትስበርግ አካል የሆነችው ፒንስልቫኒያ በየካቲት 16 ቀን 1952 ዓ.ም. የፕርስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን አባል፥ የእስኮትላንድና የአየርላንድ ዝርያ ከነበራቸው ቤተሰብ ተወለደ። ራስል በ15 ዓመቱ ከአባቱ ጋር በአክስዮን የልብስ መሸጫ ሱቅ ከፈተ። በዚህንም ጊዜ ነው የፕርስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያንን በመተው የማኅበረ ምዕመናን ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነው።

ይሁን እንጂ ራስል በዚህም ቤተ ክርስቲያን ይሰጡ ከነበሩት አስተምህሮዎች፥ በተለይ የዘላለም ቅጣትና በቅድመ ምዳቤ ትምህርቶች እጅግ ተቸገረ፤ በዚህም ምክንያት በ17 ዓመቱ ወደ ክህደትና መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አለመቀበል ደረጃ ደረሰ። ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ራስል በራሱ ቃል እንዲህ ብሎ ነበር፡-

1. ይህ ክፍል በአብዛኛው የተወሰደው፡- A.A. Hoekema. Jehovah's Witnesses (Eerdmans, 1963) ገጽ. 9-20 Qualified to be Ministers (Brookelyn, 1955), ገጽ 297-312 እና Jehovah's Witnesses in the Divine Purpose (Brooklyn, 1959) ገጽ 14-63 ከተባሉት የድርጅቱ መጻሕፍት ላይ ጠቅሶ ከጻፈው ጽሑፍ ላይ ነው

"በፕርስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮአዊ ቀኖና ሥር ያደኩ ሰው ብሆንም በተፈጥሮዬ የሚጠይቅ አእምሮ ስለነበረኝ በአመክንዩ እውነታ ትምህርቶቹን መዘንኩአቸው፤ በዚህም ምክንያት የእምነቴ ታንኳ በእግዚአብሔርና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተሰበረ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ዝግጅትና ምሪት ጉዳዩ ወደ በጎ ጎዳና መራኝ። ይልቁንም በሰዎች የሃይማኖት መግለጫ ሁሉና በቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ ላይ የነበረኝ ተአማኒነት ተሰበረ"[2]

በ1870 ዓ.ም.፡—

"ለመጀመሪያ ጊዜ ከጆናስ ዊንደል ስለ አድቬንቲስቶች ሰማሁ። የዚህ ሰው ቃለ እግዚአብሔር አተረጓጎም ሙሉ በሙሉ እኛ፥ አሁን እየተደሰትንበት ባለው መልኩ ግልጽ ባይሆንም ከእግዚአብሔር በታች በቂ ነበር። ይህም ነበር በመዋዥቅ ላይ የነበረውን እምነቴን በእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል ያበረታው"[3]

ከዚያም ራስል በፒትስበርግ ስድስት ሰዎች የሚገኙበትንና በየጊዜው ለመገናኘት የወሰነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ከ1870 ዓ.ም. — 1875 ዓ.ም. አደራጅቶ መራ። ራስልና ጓደኞቹ ክርስቶስ በሥጋ ዳግም ይመጣል የሚለው ትምህርት ስላልተዋጠላቸው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት መንፈሳዊና የማይታይ መሆኑን ለማሳመን ራስል "ዘ ኦብጀክት ኤንድ ማነር ኦፍ ዘሎርድስ ሪተርን" በሚል ርዕስ 50ሺ ቅጂ በራሪ ወረቀቶችን አባዛ።

በ1876 ዓ.ም. ራስል ከሮቸስተሩ ኤን ኤች ባርባር ጋር ተገናኘ፤ ባርቦር ከአድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ያፈነገጡ ሰዎች መሪ ነበር። ያፈነገጡበትም ምክንያት ራስል የክርስቶስ ዳግም ምጽአት መንፈሳዊ (የማይታይ) ነው በሚለው ትምህርቱ በማመናቸው ነበር። ከዚያም ራስል ይመራው የነበረው የፔትስበርግ ኅብረትና ባርቦር ይመራው የነበረው የሮቸስተር ኅብረት ተቀላቀለ። በዚህም ግንኙነት ምክንያት "ዘ ሄራልድ ኦፍ ዘ ሞርኒንግ" መጽሔት የመውጣት ምክንያት ሆነ። ይህ መጽሔት በፊት በባርቦር ነበር የሚታተመው። በ1877 ዓ.ም. ባርቦር

2. Watchtower magazine, 1916, ገጽ. 170-171 ከJehovah's Witnesses in the Divine Purpose, ገጽ. 14 ላይ ጠቅሶ ከወሰደው። ለምን ግን "በሁሉም" የሃይማኖት መግለጫዎች ላይ የነበረው ተአማኒነት ተሰበረ?

3. Jehovah's Witness in the Divine Purpose, ገጽ. 14



እና ራስል በኅብረት 194 ገጽ ያለውን መጽሐፍ፡— "ስሪ ወርድስ ኦር ፕላን ኦፍ ሪደምሽን" አሳተሙ።

"ይህ መጽሐፍ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በ1874 ዓ.ም. የተፈጸመ ሲሆን ምጽአቱም ሳይታይ በመንፈስ ነው የሚለውን እምነታቸውን ገሃድ አደረገው። ከዚያም በትክክል በሚያስደንቅም ሁኔታ የአሕዛብ ዘመን በ1914 ዓ.ም. እንደሚጠናቀቅ ጠቆሙ"[4]

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ራስልከባርቦር ጋር የነበረውን ግንኙነት አቋረጠ። ምክንያቱም ራስል የክርስቶስ የማዳን ሥራ አዳምንና የእርሱን ዝርያዎች ይጨምራል ብሎ ስለሚያምን ነበር። ከዚያም ራስል፡— "ዛየንስ ዋች ታወር ኤንድ ሄራልድ ኦፍ ክራይስትስ ፕረዘንስ" የሚለውን መጽሔት ማሳተም ጀመረ። የመጀመሪያው ኅትም በሐምሌ 1 ቀን 1979 ዓ.ም. ነበር ለንባብ የበቃው።

አዲሱ መጽሔት ለእንቅስቃሴው መስፋፋት ታላቅ ሚና ተጫውቶአል። ለምሳሌ፡— በ1880 ዓ.ም. በሰባት የአሜሪካን ክፍላተ አገራት 30 ጉባዔዎች ተቋቁመው ነበር። በ1881 ዓ.ም. "የመጠበቂያ ግንብ የትራክት ማኅበር" በራስል አስተዳዳሪነት ተመሠረተ። ይህ ስም በ1896 ዓ.ም. "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" በሚለው ስያሜ ተለወጠ። በታኅሣሥ 13 ቀን 1884 ዓ.ም. ይህ ማኅበር የመተዳደሪያ ደንብ በማውጣት በኮርፖሬሽን መልክ ተዋቀረ። ምን አልባት ይህን ቀን የድርጅቱ ሕጋዊ ጅማሬ ልንለው እንችላለን። ምንም እንኳ ድርጅቱ በዚህ ስም ሕጋዊነትን ቢያገኝም 1896 ዓ.ም. የድርጅቱ ስም "የፔንሲልቫኒያው የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" የሚል አዲስ ስያሜ አገኘ[5]። በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ II ላይ እንደተጠቀሰው የድርጅቱ ዓላማ "የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በተለያዩ ቋንቋዎች በበራሪ ጽሑፎችና መጽሔቶች ወረቀቶች እንዲሁም ሕጋዊነት ባላቸው መንገዶች ሁሉ ማሠራጨት ነው"[6]

ከዚህ ዓላማ ጋር በተዛመደ መልኩ ራስል 7 ቅጽ ተከታታይ የአስተምህሮ መጽሐፍትን ጽፎአል። የመጀመሪያው ቅጽ የታየው በ1886 ዓ.ም. ሲሆን የመጽሐፉም ርዕስ "ዘ ዲቫይን ፕላን ኦፍ ዘ ኤጅ" የሚል ነበር። ሰባቱም ቅጽ መጻሕፍት በመጀመሪያ የተሰየሙት "ሚሊኒያል ዳዎን" በሚል ስያሜ ሲሆን፤ በኋላም "ስተዲስ ኢን ዘ እስክሪብቸርስ" ተባሉ። እነዚህ መጻሕፍት ከፍተኛ ሥርጭት የነበራቸው ሲሆን የመጀመሪያው ቅጽ ከ6 ሚሊዮን ቅጂ በላይ ታትሞ ተሠራጭቶአል።

4. Qualified to be Ministers, ገጽ. 300

5. Qualified to be Ministers, ገጽ. 303

6. ዝኒ ከማሁ ገጽ 304

በ1889 ዓ.ም. ድርጅቱ በአልገኒ ፔንስልቫኒያ ሕንፃ አገኘ። ይህም ለ20
ዓመታት የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት ሆኖ አገልግሎአል። በ1891
ዓ.ም. ራስል የመጀመሪያ ጉዞውን በለንደን በማድረግ በ1900 ዓ.ም.
በለንደን ቢሮ ከፈተ። ወዲያው መጻሕፍትና በራሪ ጽሑፎች
(እንግሊዝኛን ጨምሮ) በተለያዩ ቋንቋዎች መታተም ጀመሩ። በ1903
ዓ.ም. ራስል ሁለተኛውን የአውሮፓ ጉዞ ወደ ጀርመን በማድረግ
የድርጅቱን ቅርንጫፍ ከፈተ። በ1904 ዓ.ም. በአውስትራሊያ ሌላ ቢሮ
ተቆረቆረ።

በ1908 ዓ.ም. በድርጅቱ የሕግ አማካሪ በሆነው ጆሴፍ ፍራንክሊን
ሮዘርፎርድ አዲስ የመስፋፋት ምዕራፍ ተከፈተ። ሮዘርፎርድ ለድርጅቱ
አንዳንድ ዕቃዎች በብሮክሊን ኒውዮርክ ስለገዛ ዕቃዎቹን በይዞታነት
ለማቆየት ድርጅቱ ሌላ ኮርፖሬሽን አዋቀረ። በዚህም ምክንያት
"ፒውፕልስ ፑልፒት ኮንሶሌሽን ኦፍ ኒውዮርክ" ተቆረቆረ። በ1956
ዓ.ም. የዚህ ኮርፖሬሽን ስም "የኒውዮርኩ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ
ቅዱስና የትራክት ማኅበር" ተባለ።

በአንድ ወቅት ራስል በመጽሔቱ "ታምረኛው ስንዴ" አንዱን
ፓውንድ በአንድ ጆላር ሊሸመት እንደሚችል ይህም ስንዴ
ከመደበኛው ስንዴ በአምስት እጥፍ እንደሚያድግ አስተዋውቆ
[Advertise] ነበር። በዚህም ምክንያት የ"ብሮክሊን ዴይሊ ኢግል"
መጽሔት "ፓስተሩና" "ተአምረኛው ስንዴ" በሚል፥ አስቂኝ የካርቶን
ስዕል አውጥቶበት ነበር። በዚህም ምክንያት ራስል የመጽሔቱን አዘጋጅ
በፍርድ ቤት ስለከሰሰው መንግሥት ስንዴውን ለማስመርመር ተገዶ
ነበር። ነገር ግን እውነታው የተገላበጠ ሆነ። ይኸውም "ታምረኛው
ስንዴ" ከሌሎች ስንዴዎች አምስት እጥፍ የተሻለ ሳይሆን ከሌሎቹ
በጥቂት ያነሰ ሆኖ ተገኘ። ከዚህም የተነሣ የኤግል መጽሔት አዘጋጅ
ክሱን ረታ። ፍርድ ቤቱም በነጻ አሰናበተው[7]።

ራስል በ1979 ዓ.ም. ሚሪያ ፍራንሴስ አክሊን አገባ። በዚህ ጋብቻ
ራስል ልጅ አልወለደም። ሚስስ ራስል ለብዙ ዓመት በመጠበቂያ
ማኅበር ገንዘብ ያዥና ጸሐፊ፥ የ"መጠበቂያ ግንብ" መጽሔት ረዳት
አዘጋጅ ሆነው ሠርተዋል። በ1897 ዓ.ም. ራስልና ወይዘሮዋ ተፋቱ።

7. Walter R. Martin እና Norman H. Klann <u>Jehovah of the Watchtower</u>, rev. ed. (Grand Rapids: Zondervan, 1959) ገጽ 15-77 ከኅዳር 1 ቀን 1916 ዓ.ም. ከወጣው <u>Daily Eagel</u> ላይ ጠቅሰው እንደጻፉት።



በ1913 ዓ.ም. ሚስስ ራስል "ባላቸው ያደረግባቸው ስለነበረው ጭቆና፥
ከሌሎች ሴቶች ጋር የነበረው አላስፈላጊ ግንኙነት" በመጥቀስ ራስልን
ከሰሱ[8]።

ራስል የጻፋቸውን የአስተምህሮ መጻሕፍት ቃለ እግዚአብሔርን
ለመረዳት ብቸኛ አማራጮች እንደሆኑ እንዲያውም ያለ እነርሱ አንድ
ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ መረዳት ስለማይችል በመንፈሳዊ
ጨለማ ውስጥ እንደሚቆይ በድፍረት የተናገረ ሰው ነው። ቃል በቃል
የራስልን አባባል እናቅርብ፡-

> "የተረዳነው ነገር አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ
> መለኮታዊውን ዕቅድ ማወቅ አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን ጥቂት
> እንኳን ተጠቅሞባቸው የኔን መጽሐፍ ማቆም [ወደ ጎን
> ማድረግ] ትውስታቸውን ወይንም ትምህርታቸውን በመርሳት
> ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ መመለስ በሁለት ዓመት ውስጥ
> ጨለማ ውስጥ እንደሚያስገባ ነው፤ ከልምምዳችን የተረዳነው።
> በሌላ አነጋገር አንድ ሰው "እስክሪብቸርስ እስተዲስ" [የራስል
> 7 ቅጽ መጻሕፍት] ብቻ ከነማጣቀሻቸው ያነበበ፥ መጽሐፍ
> ቅዱስን ባያነብ እንኳን፥ በሁለት ዓመት ውስጥ ወደ ብርሃን
> ይወጣል። ምክንያቱም የቅዱሳት መጻሕፍት ብርሃን በእጁ
> አለና"[9]

በአንድ ወቅት ለራስል "የግሪክ ፊደላትን ታውቃለህ?" የሚል ጥያቄ
ሮስ ላውየር ከተባለ ሰው ቀርቦለት ነበር። ራስልም፡- "እንዴታ! በደንብ
አውቃለሁ እንጂ" የሚል መልስ ሰጠ። በኋላም የግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ
ተሰጥቶት ከላይ ያሉትን ፊደላት እንዲጠራቸው ቢጋበዝ ሊጠራቸው
ስላልቻለ የግሪክ ቋንቋን ያለመቻሉን አምኖ ነበር[10]።

ራስል በጥቅምት 31 ቀን 1916 ዓ.ም. በቴክሳስ ክፍለ አገር ሞተ።
ይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት ራስል በሕይወቱ ዘመን አንድ ሺ
ማይሎችን በመሄድ 30ሺ ስብከቶችን የሰበከ በድምሩ ከ50ሺ ገጽ በላይ
ወረቀቶችን የጻፈ ሰው ነበር[11]።

8. Bruce M. Metzger, "The Jehovah's Witnesses and Jesus Christ" <u>Theology Today</u>, April, 1953, ገጽ. 65-66 ዶ/ር ሜትዚገር ለአንባቢያቸው የጠቀሱት ከ Herbert H. Stroup's. <u>The Jehovah's Witnesses</u> (New York: Columbia University press, 1945), ገጽ 9-11 ላይ ነው።
9. <u>Watchtower</u>, Sept. 15,1910 ገጽ. 298 እንዲሁም ይህ ክፍል በ July, 9157 <u>Watchtower</u> ላይ ተጠቅሶ ይገኛል። በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
10. Russel – Vs – Ross transoript on file in the Brooklyn headquarters of the Watchtower Society. Martin & Klann ገጽ. 18 ላይ ጠቅሰው እንደጻፉት።
11. <u>Qualified to be Ministers</u>, ገጽ. 310



## “ዳኛው” ጆሴፍ ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ (1869–1942)

በራስል የአስተዳደር ዘመን የድርጅቱ የሕግ አማካሪ የነበረው ጆሴፍ በራስል የአስተዳደር ዘመን የድርጅቱ ሁለተኛ ፕሬዝዳንት ሆነ። ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ የድርጅቱ ሁለተኛ ፕሬዝዳንት ሆነ። ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ የባፕቲስት ቤት ክርስቲያን ሮዘርፎርድ በኅዳር 8 ቀን 1869 ዓ.ም. የባፕቲስት ቤት ክርስቲያን አባል ከነበሩ ቤተሰብ በቦንቬል ሚዞሪ ተወለደ። የ16 ዓመት ልጅ ሳለ የሕግ ትምህርት ለመማር ኮሌጅ ገባ። በ22 ዓመቱ በፍርድ ቤት በዳኝነት መሥራት ጀመረ። በቦንቬል ፍርድ ቤት ለአራት ዓመት ከሠራ በኋላ ዋናው ዳኛ በሚታመምበት ጊዜ እንደ ዋና ዳኛ ሆኖ አገልግሎአል። ለዚህም ነው ሮዘርፎርድ “ዳኛው” የተባለው። ሮዘርፎርድ ከመጠበቂያ ግንብ ባለሥልጣናት ጋር ግንኙነት የጀመረው በ1894 ዓ.ም. ነበር። ወደ እንቅስቃሴው የገባው በ1906 ዓ.ም. ሲሆን፤ የድርጅቱ የሕግ አማካሪ የሆነው በ1907 ዓ.ም. ነው።

ሮዘርፎርድ የፕሬዝዳንትነቱን ወንበር እንደያዘ የብሮክሊኑን ቢሮ የአስተዳደር መዋቅር በመቀየር የድርጅቱ አባላት ወደ መስክ አገልግሎት እንዲያተኩሩ አደረገ። ነገር ግን ራስል በሞተ ማግስት በድርጅቱ ባለሥልጣናት መካከል የሥልጣን ሽኩቻ ተፈጠረ የችግሩ ምክንያት ናችሁ የተባሉትም ሰዎች ከሥልጣናቸው ተባረሩ።

በሐምሌ 1917 ዓ.ም. ከራስል 7 ቅጽ ተከታታይ መጻሕፍት መካከል የመጨረሻው ጥራዝ “ዘ ፊኒሽድ ሚስትሪ” በሚል ርዕስ ታተመ። ይህ መጽሐፍ ራስል በሕይወት ዘመኑ በራእይና በሕዝቅኤል መጻሕፍት ላይ የጻፋቸውን ማብራሪያዎች በማሰባሰብ በመጠበቂያ ግንብ ዋና አዘጋጆች ለኅትመት የቀረበ ነበር። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ “ዘ ፎል ኦፍ ባቢለን” [“የባቢሎን ውድቀት”] በሚል ርዕስ በአራት ገጽ የተጻፈው በበራሪ



ጽሑፍ መልክ በብዛት በመታተም ከታኅሣሥ 30 ቀን 1917 ጀምሮ ለቤተ ክርስቲያን አባላት ተሠራጨ። እንደዚህ በራሪ ጽሑፍ ካቶሊክና የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት የዘመኑ ባቢሎን ስለሆኑ በትልቅ መጠላት ውስጥ እንደሚያልፉ “የተነበየ” ነበር።

በየካቲት 1918 የካናዳ መንግሥት የራስልን መጻሕፍት በአገሪቱ ውስጥ እንዳይሠራጩ እገዳ አወጣ። ይህ የሆነው መጻሕፍቱ ውትድርናን አጥብቀው ስለሚከለክሉ ነበር። በግንቦት 1918 ዓ.ም. የአሜሪካን መንግሥት ሮዘርፎርድን ጨምሮ ስምንት የድርጅቱን ባለሥልጣናት የአሜሪካንን የጦርና የባሕር ሥራ አናንቃችኋል፥ ተቃውማችኋል በሚል አሠራቸው[12]።

በሰኔ 20 ቀን ያስቻለው ፍርድ ቤት ስምንቱ ሰዎች ጥፋተኛ ሆኖ ስላገኛቸው በአትላንታ ጆርጅያ በ20 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ በየነ[13]።

በዚህም ምክንያት የብሮክሊኑ ዋና መሥሪያ ቤት ሥራ ስላቆመ ድርጅቱ ሥራውን ከፒትስበርግ ማንቀሳቀስ ጀመረ። ጦርነቱ በ1918 ዓ.ም. ሲጠናቀቅ [አንደኛው የዓለም ጦርነት] የድርጅቱ አባላት የፓርላማ አባላትንና የአመራር አካላት፥ የመጠበቂያ ግንብ መሪዎች እንዲፈቱ ጠየቁ። በግንቦት 14 ቀን 1919 ዓ.ም. ስምንቱም መሪዎች በምሕረት ተለቀቁ[14]።

የብሮክሊኑ ቢሮ ዳግም ተከፈተ። በዚህም ዓመት ሁለተኛው መጽሔት “ዘ ጎልደን ኤጅ” [“ወርቃማው ዘመን”] በሚል ርዕስ ወጣ። ይህ መጽሔት በ1937 ዓ.ም. ኮንሶሌሽን መጽናናት በ1946 ዓ.ም. “አዌክ” [“ንቁ”] ተባለ።

የድርጅቱ የኅትመት ሥራ እየተስፋፋ በመምጣቱ ድርጅቱ የኅትመት ሥራዎች ሁሉ በድርጅቱ ማተሚያ ቤት እንዲታተም ወሰነ። በ1921 ዓ.ም. የሮዘርፎርድ የመጀመሪያ መጽሐፍ “ዘ ሃርፕ ኦፍ ጎድ” [“የእግዚአብሔር በገና”] ወጣ። ሮዘርፎርድ ከራስልም ይልቅ ብዙ መጻሕፍትን የጻፈ ሰው ነበር። ወዲያው የራስልን መጻሕፍት የሚተኩ፥ በድርጅቱ አስተምህሮ ላይ የተመሠረቱ የአስተምህሮ መጻሕፍትን ጻፈ።

12. Qualified to be Ministers, ገጽ. 315.
13. ዝኒ ከማሁ
14. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 316

በተመለከተ
በ1920 የድርጅቱ አባላት በሙሉ የመስክ ምስክርነታቸውን
ሳምንታዊ ሪፖርት እንዲያደርጉ ተወሰነ። "ለ30 ዓመት የይሖዋ
ምስክሮች ባሪያ ነበርኩ" የሚለውን መጽሐፍ የጻፈው ዊሊያም ሽነል
የእንቅስቃሴውን ውስጣዊ ሥራ እንዲህ በማለት ገልጦት ነበር፦
የሮዘርፎርድ ፖሊሲ በድርጅቱ መሠረታዊ ለውጥ አምጥቶ ነበር።
በራስል የአስተዳደር ዘመን ድርጅቱ ትኩረት የሚሰጠው በመጽሐፍ
ቅዱስ ጥናቶች፥ በባሕርይ እድገት፥ በመንፈስ ፍሬዎች ላይ ነበር።
አሁን ይህ ሁሉ ቀርቶ የድርጅቱን ጽሑፎች በማሠራጨትና ለዋናው
መሥሪያ ቤት ስለ ሥርጭቱ የየቀን ውሎ ሪፖርት ወደ ማድረግ
ተለወጠ። ሦስት አራተኛ የሚሆኑት "የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች"
[ከ1931 ዓ.ም. በፊት የነበሩት የይሖዋ ምስክሮች "የመጽሐፍ ቅዱስ
ተማሪዎች" ይባሉ ነበር] በዚህ ምክንያት ድርጅቱን ለቀቁ።

በ1931 ዓ.ም. በኮሎምበስ ኦሀዩ በተደረገው ስብሰባ የድርጅቱ አባላት "የይሖዋ ምስክሮች" ተባሉ። ይህ ስያሜ የተወሰደው ከኢሳ. 43፥10 ላይ ነው "እናንተ የመረጥሁት ባሪያዬ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል እግዚአብሔር"[15]

ከ1940 ዓ.ም. ጀምሮ "መጠበቂያ ግንብ" እና "መጽናናት" የሚባሉት መጽሔቶች በየመንገድ ዳሩ በአባላቱ መሠራጨት ጀመሩ። ይህ የማሠራጨት ፖሊሲ እስከ አሁን እንዳለ ነው [ለዚህም ነው የይሖዋ ምስክሮችን በየቤቶቻችን በሮች ላይ እና በየመንገድ ዳር የምናያቸው]።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ድርጅቱ ያወጣውን የገለልተኝነት ፖሊሲ በ1917 ዓ.ም. ዳግም አጸናው። ከዚህም የተነሣ ብዙ የይሖዋ ምስክሮች በጦር ኃይሉ ውስጥ አናገለግልም በማለታቸው ወኅኒ ተጣሉ።

ሮዘርፎርድ ድርጅቱን ለ25 ዓመት ከመራ በኋላ በጥር 8 1942 ዓ.ም. ሞተ። ድርጅቱ እንደሚለው በሮዘርፎርድ የፕሬዝዴንትነት ዘመን ድርጅቱ ከዲሞክራሲያዊ አስተዳደር በ"እግዚአብሔር ወደሚመራ" ["ቴዎክራቲክ" (Theocratic)] ድርጅት ተሸጋግሮአል። ይህም ማለት የአጥቢያ ጉባዔ ዳሬክተሮች የሚመረጡት በአጥቢያ ጉባዔዎች ሳይሆን ብሮክሊን በሚገኘው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የአመራር አካላት ይሾማሉ፤ ማለት ነው።

15. Jehovah's Witnesses in the Divine Purpose, ገጽ. 125-126





## ናታን ሆመር ኖር
## (1905–1977)

ናታን ሆመር ኖር በጥር 13 ቀን 1942 ዓ.ም. የድርጅቱ ሦስተኛ ፕሬዝዴንት ሆኖ ተመረጠ። ኖር በ1905 ዓ.ም. በቤትልሔም ፒንስልቫንያ ተወለደ። በ16 ዓመቱ የተሃድሶ ቤተ ክርስቲያን አባልነቱን በመተው አሊንቶን ፒንስልቫኒያ ወደ ሚገኘው የይሖዋ ምስክሮች ጉባዔ ተቀላቀለ። በ18 ዓመቱ የድርጅቱ የሙሉ ጊዜ ሰባኪ እንዲሁም ብሮክሊን በሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤት አባል ሆነ። በ1932 ዓ.ም. የድርጅቱ የኅትመት እንቅስቃሴዎች ሁሉ አስተባባሪ እንዲሁም የኅትመት ቢሮ አስተዳዳሪ ሆነ። በ1934 ዓ.ም. የኒውዮርክ ኮርፖሬሽን ዳሬክተር፤ 1940 ዓ.ም. የፒንስልቫኒያው ኮርፖሬሽን ምክትል ዳሬክተር ሆነ።

ኖር ከእርሱ በፊት እንደነበሩት ፕሬዝዴንቶች ዕውቅ አልነበረም። ከአሜሪካን ውጪ ያሉ አንዳንድ የድርጅቱ አባላት ስሙን እንኳ አያውቁም ነበር። በሥልጣን በነበረበት ጊዜ ዓላማው አድርጎ የተንቀሳቀሰው የትምህርት ፕሮግራሞችን ማሳደግ ነበር። ይህም እውን የሆነው የ"ጊልአድ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት" በ1943 ዓ.ም. ሲቀረቀር ነው። ሌላው የአጥቢያ ጉባዔ የሥልጠና ፕሮግራሞችን የሚያግዝ ሦስት የመማሪያ መጻሕፍትን በ10 ዓመታት ውስጥ ማዘጋጀት ነው። እነዚህ መጻሕፍት ያካተቱት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች፥ የመመስከር ዘዴና ታሪክን ነው። እነዚህም መጻሕፍት፦ "ቴዎክራቲክ ኤይድ ቱ ኪንግደም ፐፐልሸርስ" (በ1945 ዓ.ም.) "ኢክዩፐድ ፎር ኤቨሪ ጉድ ወርክ" (በ1946 ዓ.ም.) እንዲሁም "ኳሊፋይድ ቱ ቢ ሚኒስተርስ" (1955 ዓ.ም.) የሚባሉት ናቸው።

እነዚህ መጻሕፍት ሌላ በኖር የፕሬዝዴንትነት ዘመን አዲስ የአስተምህሮ መጻሕፍት ተጽፈዋል። ከዚህም በፊት እንደነበሩት የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች እነዚህ መጻሕፍት በአንድ ግለሰብ የተጻፉ አልነበሩም በመሠረቱ እነዚህ መጻሕፍት በሚስተር ኖር ተጽፈው ከኅትመት በፊት የተለያዩ ሰዎች አይተዋቸዋል። ከዚያም የጽሐፊው ስም ሳይኖር ለኅትመት በቁ[16]። እነዚህ መጻሕፍት ራስልና ሮዘርፎርድ የጻፎአቸውን የአስተምህሮ መጻሕፍት የተኩ ነበሩ። ከእነዚህም መካከል በ1943 ዓ.ም. የታተመው "እውነት አርነት ያወጣሃል" እንዲሁም በ50 ቋንቋዎች 17 ሚሊየን ቅጂ ተባዝቶአል የሚባለው "እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን" የሚለው ይገኙበታል።

በኖር የፕሬዝዴንትነት ዘመን ከተሠሩት ሥራዎች መካከል ወደ እንግሊዝኛ ተተርጎመ የሚባለው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይህ መጽሐፍ በመጀመሪያው የታየው 1950 ዓ.ም. ሲሆን "ዘ ኒው ወርልድ ትራንስሌሽን ኦፍ ዘ ክርስቲያን ግሪክ እስክሪብቸር" [የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም] በመባል ይጠራል። የብሉይ ኪዳን ኅትሙ የወጣው ቀስ በቀስ ነበር። የመጀመሪያው ጥራዝ የታተመው በ1953 ዓ.ም.፥ ሁለተኛው በ1955 ዓ.ም.፥ ሦስተኛው በ1957 ዓ.ም.፥ አራተኛው በ1958 ዓ.ም.፥ አምስተኛው በ1960 ዓ.ም. ነበር። "የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም" ሙሉ ጥራዝ ለመጀመሪያ የታየው በ1961 ዓ.ም. ነበር። የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚ አባላት እነማን እንደሆኑ፥ ከመጀመሪያው ቅጂ (በኩረ-ጽሑፍ) ወደ እንግሊዝኛ የመተርጎም አቅማቸውና ዕውቀታቸው ምን ያህል እንደሆነ እስከ ዛሬ በድርጅቱ የተሰጠ ማብራሪያ የለም። ነገር ግን ዕብራይስጥና የግሪክ ቋንቋ ሊቃውንት ትርጉሙን በአንድ ድምፅ ኮንነውታል።

16. ይህ መረጃ የተገኘው የሚስተር ኖር ጸሐፊ ከነበሩት ሚስተር አሊስ ቪ ግላስ ብሮክሊን በሚገኘው ዋና ጽሕፈት ቤት በሐምሌ 6 ቀን 1962 ዓ.ም. ቃለ መጠይቅ ተደርገው መሆኑን A.A Hoekema, Jehovah's Witnesses በሚለው መጽሐፍ ገጽ 18 ላይ ጠቅሶ ጽፎአል።





## ፍሬድሪክ ዊሊያም ፍራንዝ (1893–1992)

ናታን ሆመር ኖር በ1977 ዓ.ም. ሲሞት በእርሱ የፕሬዝዴንትነት ዘመን እንደ ትልቅ የሥነ-መለኮት ምሁር ይቆጠር የነበረው ፍሬድሪክ ዊሊያም ፍራንዝ ሥነ-መለኮትን በአግባቡ የተማረ ባይሆንም ከእርሱ በፊት ከነበሩት የድርጅቱ ፕሬዝዴንቶች ይልቅ የሥነ-መለኮት ዕውቀት የነበረው ሰው ነበር። በዚህ ሰው የአስተዳደርም ዘመን ነው የይሖዋ ምስክሮች ለትምህርታቸው ማስረጃ የሚሉአቸውን ጥቅሶች መጥቀስ የጀመሩት።

ከ1980 ዓ.ም. ጀምሮ ድርጅቱ ታላቅ ቀውስ ውስጥ ስለ ወደቀ ብዙ የአስተዳደር አካላት የፍራንዝ የወንድም ልጅ፥ ሬሞንድ ፍራንዝን ጨምሮ ለድርጅቱ ታማኝ አይደላችሁም በሚል ከሥራ ተባረሩ። ነገር ግን ነውጡን ያስከተሉት ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከነዚህም ውስጥ የድርጅቱ መሠረታዊ አስተምህሮቶች ጥያቄ ውስጥ የመውደቃቸው ጉዳይ ዋነኛው ነበር። ለምሳሌ፡- ድርጅቱ ሥነ-ፍጻሜን በተመለከተ ያወጣቸው አሀዛዊ ትንቢት [አርማጌዶን ጦርነት በ1975 ዓ.ም. ይሆናል] በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ማጣቱ፥ ዳግም ልደት ለ144ሺዎች ("ለቅቡዓን") ብቻ እንጂ ለበጎች አያስፈልግም የሚለውን ትምህርት ጥቂት የአመራር አካላት፥ ሬይ ፍራንዝን ጨምሮ፥ ማውገዛቸው ይገኝበታል[17]።

ፍራንዝ በ1992 ዓ.ም. ሲሞት አሁን የእርሱን የፕሬዝዴንትነት ቦታ ተክቶ ያለው በፍራንዝ የአስተዳዳሪነት ዘመን የአመራር አካል የነበረው ሚልተን ጂ ሔንሼ ነው።

17. Robert M. Bowman, Jr. Jehovah's Witnesses. P 12.

## 2.6 የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ

### ሀ. ሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ አጠቃላይ ቅኝት

“ሁሉም የይሖዋ ምስክር ይሰብካል” የሚለው የአጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ[1] ሽማግሌ አነጋገር የይሖዋ ምስክር መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአጭሩ የሚገልጽ የማጠቃለያ ዐረፍተ ነገር ነው። አንድ ሰው የይሖዋ ምስክሮች ንቁ ተሳታፊ አባል የሚሆነው የይሖዋ ምስክሮችን መልእክት “ሲያስፋፋ” [“Publishing”] ብቻ ነው። ለዚህም ነው ንቁ ተሳታፊ አባል “አስፋፊ” [“Publisher”] በሚል ስያሜ የሚጠራው።

አንድ ንቁ የይሖዋ ምስክር በወር 18 በዓመት 236 ሰዓታትን “በመስክ አገልግሎት”[2] ላይ ያሳልፋል[3]። ይህ ሰዓት አንድ ንቁ አባል “ጉባዔ”[4] የሚካፈልበትን የድርጅቱን ጽሑፍ የሚያነብበትን፥ አዳዲስ አባሎችን የመጠበቂያ ግንብ ማኅበርን[5] አስተምህሮ የሚያስተምርበትን ጊዜ ሳይጨምር ነው። ሙሉ ጊዜያቸውን በመስክ አገልግሎትና በድርጅቱ ሥራ ላይ የሚያሳልፉት “አቅኚዎች” [“pioneers”] ይባላሉ። አስፋፊዎች ምንም ዓይነት ክፍያ ከድርጅቱ አይከፈላቸውም። አቅኚዎች ግን “መጠነኛ” ክፍያ ያገኛሉ። የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ተከታዮቹን አቅኚና አስፋፊ ብሎ ይከፍላቸው እንጂ እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር የድርጅቱ የሙሉ ጊዜ ሠራተኛ ነው ቢባል እብለት አይሆንም።

ዓለማቀፋዊ የሆነው የሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ የሚደራጀው ብሮክሊን በሚገኘው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት በኩል ነው። በእያንዳንዱ የአጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ ውስጥ ሁለት ሣጥኖች ይገኛሉ። አንዱ ሣጥን በየአገሩ ለሚገኙ አጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ ግንባታ የሚውል ስጦታ የሚሰጥበት ሲሆን ሁለተኛው ሣጥን ደግሞ ዓለማቀፋዊ የሆነውን ሚሲዮናዊ ሥራ የሚደግፍ ስጦታ የሚጨመርበት ነው። የይሖዋ ምስክሮች ስጦታቸውን በእነዚህ ሣጥኖች ውስጥ እንዲጨምሩ ድርጅቱ ያበረታታል[6]።

1. የይሖዋ ምስክሮች የመሰብሰቢያ ስፍራቸውን “የመንግሥት አዳራሽ” [Kingdom Hall] ብለው ይጠሩታል።
2. “የመስክ አገልግሎት” የሚባለው በየመንገድ ዳሩና በየቤቱ የመጠበቂያ ግንብ ወንጌልን መስበክና ጽሑፉን ማሠራጨት ነው።
3. Robert M. Bowman Jr. Jehovah's Witnesses. (Grand Rapids: Zondervan Publishing House, 1995) ገጽ. 14
4. የሰንበት ስብሰባ “ጉባዔ” በመባል ይታወቃል።
5. የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት፡- “የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር” በመባል ይታወቃል።
6. ለዚህ ጽሑፍ ዝግጅት ዶ/ር ስቲቨ ስትራውስ ቃለ መጠይቅ ያደረጋቸው በአሜሪካን አገር የሚገኙ የአጥቢያ ሽማግሌ እንደሚሉት፡- በአብዛኛው አጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ ድርጅቱን የሚረዳው ለሚሲዮናውያን የገንዘብ መዋጮ በማድረግ ነው።



በየሳምንቱ እያንዳንዱ የአጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ ሳምንታዊ “የአገልግሎት ስብሰባ” [Service Meeting] ይኖረዋል። በዚህ የስብሰባ ጊዜ በየአገሩ ያሉት የይሖዋ ምስክሮች የሥራ ዜና ያዳምጣል። “የመንግሥታችን አገልግሎት” [Our Kingdom Ministry] ከሚባለው ጋዜጣ “ቴዎክራሲያዊ ዜና” [Theocrtic News] የሚባለው አምድ ይነበባል። በየሳምንቱ እያንዳንዱ የአጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ ተመሳሳይ ርዕስ ያጠናል። ስለዚህም እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር በየአገሩ የይሖዋ ምስክሮች የሥራ እንቅስቃሴ እንዲያውቅ ይረዳዋል።

እያንዳንዱ ሚሲዮናዊ ከመጣበት የአጥቢያ ጉባዔ ጋር ግንኙነት ማድረግ ይችላል። ነገር ግን ይህ ግንኙነት ሕጋዊ አይደለም። ሕጋዊ የሆነው ግንኙነት ከዋናው ጽሕፈት ቤት ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ብቻ ነው። የሚሲዮናውያንን የሥራ ሪፖርት የሚያሠራጨው ዋና ጽሕፈት ቤቱ ነው።

የይሖዋ ምስክሮች ሚሲዮናዊ ሆነው በሌላ አገር እንዲሠሩ አይገደዱም። በግለሰቡ ፍላጎት እንዲሁም “በልቡ መነሣሣት” ብቻ ነው። አንድ የይሖዋ ምስክር ወደ ሌላ አገር ሄዶ ማገልገል ቢፈልግ የሚስዮናዊ ማመልከቻ ቅጹን በመሙላት ብሮክሊን ወደሚገኘው የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት ይልካል። ድርጅቱ ግለሰቡን ከተቀበለው በሚሲዮናዊነት ወደ ሌላ አገር ከመሄዱ በፊት ጊልአድ በሚባለው የድርጅቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለአምስት ወራት ይሰለጥናል።

የጊልአድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በ1943 ዓ.ም. ሲከፈት ዓላማ ያደረገው “የሙሉ ጊዜ አቅኚ አገልጋዮችን በውጪ አገር ሚሲዮናዊ ሆነው እንዲያገለግሉ ለመርዳት ነው።”[7] የጊልአድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሥርዓተ ትምህርት ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቢሆንም የስብከት ዘዴንና የድርጅቱን ድርጅታዊ አወቃቀር በተጓዳኝነት ያስተምራል። ትምህርቱን ለአምስት ወራት ተከታትለው የጨረሱትን ዋናው መሥሪያ ቤት በሚሲዮናዊነት ወደተለያዩ አገሮች ይልካቸዋል።

ጊልአድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በአንድ ጊዜ 50 ተማሪዎችን ተቀብሎ የማስተማር አቅም አለው። የበለጠ ሚሲዮናውያንን ለማሠልጠን በኒውዮርክ ፓተርስን ፋርም በሚባለው አካባቢ አዲስ ሕንፃ እየገነባ ነው።

7. Doing God's Will (1986) ገጽ. 22

አብዛኛውን ጊዜ ሚሲዮናውያኑ የሚችሉትን ቋንቋ በሚናገሩበት አካባቢ ይመደባሉ። ነገር ግን ቋንቋውን በማይችሉበት አካባቢ የተመደቡት ሚሲዮናውያን ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ቋንቋ ይማራሉ። የሚሲዮናውያኑን የመጓጓዣ ወጪ፥ የቤት ክራይ፥ የምግብና አንዳንድ የተለያዩ ወጪዎችን የሚሸፍነው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ነው። ሚሲዮናውያኑ በወር 140 ሰዓታትን በመስክ አገልግሎትና መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት ማሳለፍ ይጠበቅባቸዋል[8]። የሁሉም የይሖዋ ምስክሮች የመስክ አገልግሎት ትኩረት ያደረገው የይሖዋ ምስክር ባልሆነ ማንኛውም ግለሰብ ላይ ነው[9]። የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ሚሲዮናውያኑ ሥራቸውን የዕድሜ ልክ እንዲያደርጉት ያደፋፍራል።

## ለ. የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ በኢትዮጵያ[10]

### የመጀመሪያው የይሖዋ ምስክር በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የይሖዋ ምስክር ነው የሚባለው ኪሪኮር አታዛኮርታዚያን [Krikor Hatzakortazian] ነው። አታዛኮርታዚያን አርሜኒያዊ ይሁን እንጂ ከየት እንደመጣ፥ እንዴት የይሖዋ ምስክር እንደሆነ የሚታወቅ ነገር የለም። አታዛኮርታዚያን በ1935 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የይሖዋ ምስክር ቢሆንም ብሮክሊን ከሚገኘው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የተላከ የድርጅቱ ሚሲዮናዊ አልነበረም። ይህ ሰው የአርሚኒያ፥ የግሪክና የፈረንሳይ ቋንቋ ተናጋሪ ነበር። “የማስፋፋት” ሥራውን እንደ ጀመረ ነበር “ስደት” የገጠመው። በኅዳር 1 ቀን 1935 ዓ.ም. በወጣው “መጠበቂያ ግንብ” በመባል በሚታወቀው የድርጅቱ መጽሔት ላይ የመጀመሪያውን ይመስክ አገልግሎት እንዲህ አድርጎ ገልጾት ነበር፡-

“ከሥራ ወደ ቤቴ ስመለስ ከሰይጣን ወኪሎች አንዱ ከተደበቀበት ስፍራ በድንገት በመውጣት ጭንቅላቴን በትልቅ በትር ሁለቴ መታኝ። የመታኝም አጠንክሮ ስለነበር በትሩ ለሁለት ተሰበረ። ነገር ግን በጌታ እርዳታ፥ ለጎረቤቶቼም መደነቅ ቁስሌ ሥር የሰደደ አልነበረም። በሌላ ጊዜ ደግሞ የጠላት ላይ የቆየሁት ለሁለት ቀናት ብቻ ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ የጠላት ወኪል በጩቤ አጠቃኝ። ነገር ግን ሊወጋኝ ባለበት ቅጽበት ባልታወቀ ኃይል ጩቤውን በመወርወር ብቻዬን ተወኝ”።

8. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 23

9. ይህ የሆነበት ምክንያት ይሖዋ ምስክር ሆኖ በመጠበቂያ ግንብ የሃይማኖት ድርጅት ጥላ ሥር ካልተጠለለ የዘላለም ሕይወት የለውም የሚል ጽኑ እምነት ስላላቸው ነው።

10. አብዛኛውን መረጃ የወሰድነው ዶ/ር ስቲቨ ለትራውስ “የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ በኢትዮጵያ” በሚል ርዕስ በ1993 ዓ.ም. ከጻፈው ያልታተመ የእንግሊዝኛ ጽሑፍ ላይ ነው። ይህ ታሪክ በወቅቱ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴራሲዮን የነበረችውን ኤርትራን የሚጨምር ነው።



“ነገር ግን አሁንም ስደታቸውን ገፍተውበት ነበር። በዚህ ጊዜ ደግሞ በሐሰት ወንጅለውኝ በአጼው ፊት ለመቅረብ ወደ መዲናዋ፥ አዲስ አበባ ልከውኝ ነበር። በከተማዋ በቆየሁባቸው ጊዜያት (አራት ወር) በተለያዩ ስፍራዎች በመዘዋወር በየቤቱ፥ በየሆቴል ቤቶችና በየካፍቴሪያዎች አገልግሎት እሰጥ ነበር። በመጨረሻም በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀረብኩ፤ ካዳመጡኝም በኋላ ጥፋት ስላላገኙብኝ ወደ ቤት እንድሄድ በማዘዝ በነፃ አሰናበቱኝ። ስለዚህ ድል ጌታ ይመስገን!”[11]

በመጠበቂያ ግንብ ዋና መሥሪያ ቤት ተልከው፥ አገራቸውን ለቀው ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የመጀመሪያዎቹ ሚሲዮናውያን ኢትዮጵያ የደረሱት በ1950 ዓ.ም. ነበር። “እንደ እናንተ ይናገራል ስለሚባለው የድሬዳዋ ሰው አንዳንድ ወሬ ሰሙ” ። ከሚሲዮናውያኑም አንዱ፡- ሃይውርድ ዋርድ [Haywood ward] ወደ ድሬዳዋ ተጓዘ እዚያም “እንግሊዝኛ መናገር የማይችል አንድ ሽማግሌ ሰው አገኘ። ሚሲዮናዊ እንደመሆኑ መጠን ራሱን አስተዋወቀ። ሽማግሌው እንባቸውን እንዥረዥሩት፤ ወደ ሰማይ አንጋጠው በአርሜኒያ ቋንቋ አጉተመተሙ። በንግግራቸው መካከል ጆሆቫ የሚለው ስም ነበር። ይህ ሰው ወንድም አታዛኮርታዚያን ነበር”[12]። ለሚሲዮናዊውም በእጃቸው የቀሩትን የመጠበቂያ ግንብ መጽሔት የጥንት ቅጂ አሳዩት። ሚሲዮናዊው ዳግም ወደ ድሬዳዋ ከመመለሱ በፊት ነበር አታዛኮርታዚያን የሞቱት። ከዚህም የተነሣ አታዛኮርታዚያን እንዴት የይሖዋ ምስክር እንደሆኑ፥ እንዴት ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ሳይታወቅ ቀረ። ነገር ግን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት በኢትዮጵያ የነበሩ የይሖዋ ምስክር አታዛኮርታዚያን ናቸው[13]።

## በቅንጅት የመጀመሪያው ሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ

ሚሲዮናዊነትን ዓላማቸው አድርገው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት የመጀመሪያዎቹ የይሖዋ ምስክሮች በጊልአድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የተማሩ ሦስት ያላገቡ ሚሲዮናውያን ነበሩ። ዲን ሆብት እና የይውድ ዋርድ በመስከረም 14 ቀን 1950 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ

11. Year book 1992. ገጽ. 82

12. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 81

13. ዝኒ ከማሁ ገጽ 80-82

በመምጣት[14] የመጠበቂያ ግንብን ሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ ጀመሩ[15]። እነዚህ የመጀመሪያዎቹ ምስት ሚሲዮናውያን ዓላማ አድርገው መንቀሳቀስ የጀመሩት "አንድ ሰው አንድ ያግኝ" በሚል ነበር። በአንድ ዓመት ውስጥም ስድስት ኢትዮጵያውያን ንቁ ተሳታፊ አባል በመሆን ተመዘገቡ። በዓመቱም ማለቂያ አካባቢ ቁጥራቸው ወደ አሥራ ስድስት ደረሶ ነበር[16]።

የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ አስፋፊ ከሚሲዮናውያኑ አንዱ በመንገድ ዳር ያገኘው ወጣት ነበር። የይሖዋ ምስክሮቹ ሚሲዮናውያን እንደሆኑ ስላወቀ እርሱ ራሱ ጌታዬ እባክህ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ንገረኝ አለው። ሚሲዮናዊውም ወደ ቤቱ ወስዶት "ሌት ጎድ ቢ ትሩ" [እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን] የሚለውን መጽሐፍ አስጠናው። በማግስቱም፥ በነበራቸው የጥናት ጊዜ ኢትዮጵያዊው አንድ ጓደኛውን ይዞ መጣ። በየዓመቱም መጨረሻ ላይ እነዚህ ሁለት ሰዎች ቅንዓት የነበራቸው ንቁ የይሖዋ ምስክር ሆኑ። እያንዳንዳቸውም በሚመሩት ሳምንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ከ20 ሰዎች በላይ ተካፋዮች ነበሩ[17]።

በቅንጅት የተጀመረውም ሚሲዮናዊ ሥራ ተቃውሞ የነበረበት ነበር። ሚሲዮናውያኑ እንዲህ በማለት ሪፖርት አድርገው ነበር፡-

> "ጥንታዊውና ጠንካራው የኢትዮጵያ ሚሲዮናዊው ድርጅት፥ ሱዳን ኢንቲሪየር ሚሽን ምን አልባት የኛ ጠንካራው ተቃዋሚ ነው። ነገር ግን ድርጊቱ ምስክሮችን አፍርቶ ነበር። ሚሲዮኑ በአዲስ አበባ ትምህርት ቤት ነበረው። በሳምንቱ ውስጥ ሚሲዮናውያንን በማሠልጠን እሁድ ከሰዓት በኋላ ልሱዳን ሚሽን እንዲሰብኩ ይልካቸዋል። ለስብከትም የሚልካቸው ወደ ሚሲዮናውያኑ የይሖዋ ምስክር ሚሲዮናውያን ቤት እውነትን ለመማር ወደመጡት ሰዎች ነው። ከእነርሱም ውስጥ አንዱ ለእውነት ባለው አቋም ከኤስ አይ ኤም ሚሲዮን ተባረረ። ደስተኛም ስለነበር በመጀመሪያው ወር አገልግሎቱ 40 ሰዓት ሪፖርት አድርጓል"[18]።

14. Year book 1992, ገጽ 95-96
15. Awake . 1960, ገጽ. 21
16. Year book 1952. ገጽ. 65
17. ዝኒ ከማሁ።
18. Year book 1952 ገጽ 66 የይሖዋ ምስክሮች በመስክ ያሳለፉትን ሰዓት ለዋናው መሥሪያ ቤት ሪፖርት እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል።



በርከት ያሉ ሰዎች ወደ ሚሲዮናውያኑ ቤት መምጣት ጀመሩ። የዓመቱንም ሚሲዮናዊ ሥራ በሚያበረታታ ሁኔታ አጠናቀቁ። ሚሲዮናውያኑ የዓመቱን ሪፖርት "ተግባራችን እስከ አርማጌዶን ድረስ እዚሁ ይቀጥል"[19] በሚል ጸሎት ደመደሙት።

ከጅማሬው አስደናቂ የሆነው ምላሽ የመጀመሪያው የመንግሥት አዳራሽ በ1953 ዓ.ም. ሲከፈትም ቀጥሎ ነበር። ሚሲዮናውያኑ፡- ኢትዮጵያውያን ለትምህርት ያላቸው ጥማትና የተማሩትንም ለማካፈል ያላቸው ፍላጎት አስደንቆናል የሚል ሪፖርት ለዋናው መሥሪያ ቤት አድርገው ነበር።

በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት፥ ኃይለ ሥላሴ በአገሪቱ ውስጥ ያሉት ሚሲዮናውያን ሁሉ በመላው ኢትዮጵያ ትምህርት እንዲጀምሩ ፈቃድ ሰጡ። ይህ ጥሪ ይሖዋ ምስክሮችንም ያካተተ ነበር። የይሖዋ ምስክሮች አዲስ አበባ በሚገኘው የንግድ ሥራ ኮሌጅ ለማስተማር መፈለጋቸው ወደ አገሪቱ የመግባት ምክንያት ሆነ ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ከነበረው "መደበኛ ፖሊሲ የተለየ"[20] ነበር። የንግድ ሥራ ኮሌጁ ታይፕ፥ የሂሳብ መዝገብ አያያዝና እንግሊዝኛ መጠነኛ ክፍያ በማስከፈል ማስተማር ጀመረ። በዚህን ወቅት ከ125–13 ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ይማሩ ነበር። በ1952 ዓ.ም. ከጊልአድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የተመረቁ አዲስ ሚሲዮናውያን ወደ አገሪቱ ገቡ[21]። ወደ ተለያዩ አካባቢዎች ከመንቀሳቀሳቸው በፊት የሁለት ቀን ስብሰባ አደረጉ[22]። ዚሚራማን [Zimmermans] የተባሉት ባልና ሚስቶች ወዲያው በንግድ ሥራ ኮሌጅ ውስጥ ማስተማር ጀመሩ። ሌሎች ሁለት ባልና ሚስቶች፥ ብሩመሊ [Brumleys] እና ሉክ [Lucks] ወደ ሐረር ክፍለ ሀገር በመሄድ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከፈቱ ከሚሲዮናውያኑ ውስጥ ሁለት ያላገቡ ወንዶች በድሬዳዋ ተመሳሳይ ትምህርት ቤት ከፈቱ። ድሬዳዋ ኪሪኮር አታዛኮርታዚያን ይኖርበት የነበርች ከተማ ነች። ሁሉም ሚሲዮናውያን እምነቱን ለማስፋፋት የተጠቀሙበት ዘዴ በሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ ስበካ ማካሄድ ሳይሆን ከትምህርት ክፍለ ጊዜ በኋላ ፈቃደኛ ተማሪዎችን ወደ ቤታቸው በመጋበዝ ስለ እምነታቸው ማስተማር ነበር[23]።

19. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 67
20. Awake, 1960, 21
21. Awake, 1957a, 17
22. Year book 1953. ገጽ.74
23. Year book 1992. ገጽ. 94

በ1953 ዓ.ም. ሚሲዮናውያኑ ይከተሉት የነበረውን እምነቱን የማስፋፋት ዘዴ በመቀየር በየመንገድ ዳር የተገኘውን ሰው ብቻ ሳይሆን የሰዎችንም ቤት ማንኳኳት ጀመሩ። የይሖዋ ምስክር ለመሆን ካልወሰኑ ሰዎች ጋርም የሚደረገው ጥናት እንዳይራዘም ወሰኑ።

ቤት በማንኳኳት በተካሄደ የመስክ አገልግሎት የተገኙት የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት በ1953 ዓ.ም. ተጠመቁ። በዚህ ጊዜ ነበር የወቅቱ የይሖዋ ምስክሮች ፕሬዝዴንት፥ ናታን ሆመር ኖር ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ የመጡት[24]።

የይሖዋ ምስክሮች በተለያዩ ቀለማት ያሸበረቁ፥ በሚያማምሩ ስዕሎች የተሞሉ ጽሑፎችን አዳዲስ አባሎችንም ሆነ ነባሮችን ለማስተማር ይጠቀማሉ። በ1955 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ በአጥቢያ ሚሲዮናውያን የአማርኛ ጽሑፎች ተዘጋጁ። እነዚህ አነስ ባለ መጽሐፍ የተዘጋጁት የመጀመሪያ ጽሑፎች "የእግዚአብሔር መንገድ ፍቅር ነው" እና "ይህ የመንግሥት መልካም ዜና" የሚባሉት ናቸው[25]። እነዚህ ጽሑፎች በሚሲዮናውያኑ መልዕክት በተደሰቱ ሰዎች ቤት ይቀመጡ ነበር።

ከጽሑፎቹ በተጨማሪ ሰዎችን ወደ እምነቱ ለመሳብ የተደረገው ሌላው ሙከራ፡- "አዲሱ ማኅበረሰብ በድርጊት ላይ" ["The New World Society in Action] የሚለውን ፊልም በአገሪቱ ትልቅ ሲኒማ ቤት ውስጥ ማሳየት ነበር። ማስታወቂያዎች በየስፍራው ስለተለጠፉ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩት ሰዎች ከሲኒማ ቤቱ አቅም በላይ ስለነበሩ አብዛኞቹ ፊልሙን የተከታተሉት ቆመው ነበር። ከፊልሙም በኋላ ለእያንዳንዱ ታዳሚ በራሪ ጽሑፎች ተሠራጩ። የአካባቢውን ፀጥታ ለማስጠበቅ የመጡት ፖሊሶች ጭምር ጽሑፎቹን በማሠራጨት ተባብረዋል[26]። ፊልሙ በጎንደር፥ በደሴና በአስመራ ለዕይታ ቀርቦአል[27]።

24. Year book 1952. ገጽ. 149
25. Year book 1992. ገጽ. 98-100
26. Year book 1957. ገጽ 140-141
27. Year book 1992. ገጽ. 100



በ1950ዎቹ መካከል ላይ የመጠበቂያ ግንብ ሚሲዮናውያን ከአዲስ አበባ ውጪም ሆነ ትምህርት ቤት ባቋቋሙባቸው ከተሞች እንዳይሰብኩ ተከለከሉ። ብሮክሊን የሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤት ኢትዮጵያውያኑን በአቅኚነት እያሰለጠነ ከአዲስ አበባ ውጪ ባሉ ስፍራዎች በተነ። በ1954 ዓ.ም. መጨረሻ አሥራ ዘጠኝ አስፋፊዎች በአሥራ ሦስት ከተሞችና መንደሮች ይሰብኩ ነበር። ከስድስት ሳምንት ስብከት በኋላ በአንድ ከተማ ውስጥ ሁለት ኢትዮጵያውያን አቅኚዎች አሥራ ሦስት የቤት ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን ያካሂዱ ነበር። አሥር ሰዎችም በመስክ አገልግሎት ጊዜ አብረዋቸው በመሆኑ ያስፋፉ ነበር። በ1954 ዓ.ም. አዲስ ጉባዔ ተቋቋመ[28]። እነዚህ አስፋፊዎች ወደ አዲስ አበባ በመላክ አዲስ አበባ ለሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤት የሥራ ሪፖርት ይጽፉ ነበር። የነዋሪው ሕዝብ 15000 በሚደርሳቸው ከተሞች ቢያንስ ስምንት ንቁ ተሳታፊ አባላት የሚገኙባቸው ጉባዔዎች ተቋቋሙ። በዚህ አካባቢ የሚገኝ የፕሮቴስታንት ሚስዮናዊ አንድ የይሖዋ ምስክር አቅኚ አግኝቶ እምነቱ የተሳሳተ አዲስ ሃይማኖት እንደሆነ ነገረው። አቅኚውም፥ የይሖዋ ምስክሮች አዲስ አይደሉም አቤል ራሱ የይሖዋ ምስክር ነበር አለው። ሚሲዮናዊው ለአቅኚው እምነቱ ራስልና ራዘርፎርድ የሚባሉ የሁለት ግለሰቦች እምነት እንደሆነ ነገረው። አቅኚው እነዚህን ስሞች ፈጽሞውኑ ሰምቶ እንደማያውቅ ገለጸለት። ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ የይሖዋ ምስክር ሚሲዮናዊ እንዲህ የሚል አስተያየት ሰጥቶ ነበር "ምንም እንኳ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅትን ታሪክ በቅጡ ባያውቅም እምነቱ የተመሠረተበትን የእግዚአብሔር ቃል ያውቅ ነበር"[29]።

በ1950ዎቹ መካከል አዲስ መስፋፋት ከተደረገባቸው አካባቢዎች አንዱ ኤርትራ ነው [በወቅቱ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴራሲዮን ነበረች]። ሁለት አስፋፊዎች በጤና ችግር ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ በመሄድ የመጀመሪያ ሥራቸውን ጀመሩ። በ1956 ዓ.ም. አዲስ ጉባዔ ተቋቋመ[30] ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈሉ ነበር። በ1956 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የይሖዋ ምስክር ሚሲዮናዊ ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ በመሄድ ሚሲዮናዊ ሥራ ጀመረ፥ ጽሑፎችንም ለማሠራጨት ፈቃድ አገኘ[31]።

28. Year book 1955. ገጽ 143 and Year book 1957. ገጽ. 141
29. Year book 1956. ገጽ. 141-142
30. Year book 1955. ገጽ. 143 & Year book 1957. ገጽ 36-37
31. Awake 1960. ገጽ. 21-26

በመጀመሪያዎቹ ስምንት ዓመት በኤርትራም ሆነ በኢትዮጵያ የተደረጉ ሚሲዮናዊ ሥራዎች ፈጣን እድገት የሌለባቸው ነገር ግን ብዙ ያደከሙ ነበሩ። በ1958 ዓ.ም. 128 ንቁ ተሳታፊ አባላት በስምንት ጉባዔዎች ውስጥ ይገኙ ነበር። ጉባዔዎቹ ከምዕራቡ ዓለም በመጡ ሚሲዮናውያን ሳይሆን በኢትዮጵያውያን የሚመሩ ነበሩ[32]።

## የመጀመሪያው ስደት

የይሖዋ ምስክሮች በመጀመሪያ ስደት ደረሰብን የሚሉት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነው። በ1954 ዓ.ም. የይሖዋ ምስክሮች ከመንግሥት ጥቂት ተቃውሞ ገጥሞአቸው ነበር። በዚህ ዓመት ብዙ የመጠበቂያ ግንብ ሚሲዮናውያን ወደ አገር ለመግባት ጠይቀው ጥያቄያቸው ውድቅ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን ሚሲዮናውያን የመቆየት ሕልም አጨልሞ ነበር። ከመንግሥት የደረሰባቸውን ተቃውሞ የጠነሠሱት ከመንግሥት ጋር ይሠሩ የነበሩ ሌሎች ሚሲዮናውያን ናቸው የሚል እምነት አላቸው[32]።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከውጪ የሚመጡትን ሚሲዮናውያን ሁሉ ብትቃወምም፤ የይሖዋ ምስክሮች የሥላሴን አስተምህሮ፥ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነት፥ የመንፈስ ቅዱስን ሰብእና እንዲሁም መሠረታዊ የሆኑትን የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮቶች ስለማይቀበሉ ከሌሎቹ ሚሲዮናውያን ይልቅ የይሖዋ ምስክሮችን አጥብቃ ትቃወም ነበር። በ1957 ዓ.ም. ከሌላው ጊዜ በተለየ ሁኔታ አገር አቀፍ የሆነ ተቃውሞ አስነሥታ ነበር። በሚያዝያ ወር 1957 ዓ.ም. የቤተ ክርስቲያኒቱ ዲያቆን በሰንበት ቀን ወደ ደብረ ማርቆስ ከተማ ዋና አደባባይ በመሄድ የይሖዋ ምስክሮችን አወግዞ ነበር[33]። "እነዚህ ሰዎች የማሪያም ጠላቶች ናቸው። የአሪዮስ ተከታዮች ከአገራችን ይውጡ" እያለ ጽሑፉቸውን "በእግሩ በመርገጥ" ነበር ተቃውሞውን የገለጸው። ሕዝቡም በቁጣ በመነሣሣት የይሖዋ ምስክሮች በሚሰበሰቡበት ጉባዔ ሄዶ ተቃውሞ ነበር። በዚህም ችግር ምክንያት የይሖዋ ምስክሮች በፖሊስ ጥበቃ እያሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ኮሚቴ በማዋቀር የይሖዋ ምስክሮችን አስተምህሮ መረመረ። በግንቦት 28 ቀን 1957 ዓ.ም. [ኮሚቴው የኮሚቴው ስም:- "የኢትዮጵያ ሕዝቦች ደኅንነት ባለሥልጣን" ይባላል] የሚከተለውን ትእዛዝ አወጣ:-

32. Awake 1957a. ገጽ. 28 32. Year book 1955, ገጽ.143
33. Year book 1992, ገጽ. 100



"የመጠበቂያ ግንብ ሚሲዮን ለሕዝቦች ደኅንነት አደገኛ መሆኑ ስለተረጋገጠ የዚህ ድርጅት የውጪ ሚሲዮናውያን ሁሉ እስከ ሰኔ 10 ቀን አገር ለቀው እንዲወጡ። በድርጅቱ የሚካሄዱ ማንኛውም እንቅስቃሴዎች ከላይ እስከ ተጠቀሰበት ጊዜ ድረስ እንዲያቆሙ "[34]።

አንድ መቶ ሃያ ስምንት የሚሆኑ የንግድ ሥራ ኮሌጅ ተማሪዎች ትምህርት ቤቱ ለአገሪቱ ትልቅ ጥቅም ስለሚሰጥ ተጨማሪ አስተማሪዎች እንዲመደቡ ለትምህርት ሚኒስቴር አመለከቱ። ተማሪዎቹ ከመንግሥትም ጋር በርካታ ስብሰባዎችን አደረጉ። የተማሪዎቹ አቤቱታ:- በ1955 ዓ.ም. የወጣው ሕገ መንግሥት ለሃይማኖቶች ሁሉ እኩል መብት ስለሚሰጥ የይሖዋ ምስክሮች ከአገር መባረር የለባቸውም የሚል ነው። የሃይማኖት ነጻነቱን አስመልክቶ አንድ ምክትል ሚኒስቴር እንዲህ አሉ:- "የሃይማኖት ነጻነት እንደ ምላጭ ነው። ጎልማሳ ሰው ተጠንቅቆ ይጠቀምበታል፤ ነገር ግን ሕፃናት ሰውነታቸውን ይተለትሉበታል።" የሚኒስቴሩ ምሳሌ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሃይማኖት ነጻነት ዝግጁ ያለመሆኑን የሚያመለክት ነበር። የይሖዋ ምስክሮች ግፊቱ የመጣው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነው ባዮች ናቸው[35]። ትእዛዙ ሊሻሻል ስላልቻለ ሁሉም የይሖዋ ምስክር ሚሲዮናውያን አገር ለቀው እንዲወጡ ተደረገ[36]።

ነገር ግን ሚሲዮናውያኑ በኤርትራ የመቆየት ፈቃድ ተሰጥቶአቸው ነበር። በአዲስ አበባ የነበረው ዋና መሥሪያ ቤት ስለተዘጋ ብሮክሊን የሚገኘው ዋና ጽሕፈት ቤት በኤርትራ የነበረውን ሥራ ይቆጣጠር ጀመር። "ሕይወት በአዲስ ዓለም" የሚባለው የትግርኛ በራሪ ጽሑፍ በ1957 ዓ.ም. ታተመ። ከ1958 ዓ.ም. ጀምሮ "መጠበቂያ ግንብ" የተባለው መጽሔት በትግርኛ ቋንቋ እየታተመ መውጣት ጀመረ። ጥቂት አቅኚዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ከአስመራ ከተማ ወደ ገጠር አካባቢዎች ተላኩ። በ1958 ዓ.ም. አራት ጉባዔዎች በገጠር ተቋቁመው ነበር። የይሖዋ ምስክሮች በኤርትራ የገጠማቸው ችግር ስደት ሳይሆን ሰዎች ለእምነቱ የነበራቸው ፍላጎት ሥር የሠደደ ያለመሆኑ ነው[37]።

በ1959 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መንግሥት በኤርትራ የሚገኙትን የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች እንዳይንቀሳቀሱ እንዲሁም በኢትዮጵያ ያወጣው እገዳ በኤርትራም ተግባራዊ እንዲሆን አደረገ። በ1960 ዓ.ም. ሁሉም የይሖዋ ምስክር ሚሲዮናውያን አገር ለቀው ወጡ[38]።

34. Awake 1957b, ገጽ. 17
35. Awake 1957 b, ገጽ.18-19
36. Year book 1992, ገጽ. 101
37. Year book 1958, ገጽ 77-78 & Year book 1959, ገጽ. 82-83
38. Awake 1960, ገጽ 21-26

ምንም እንኳ ከኤርትራም ሆነ ከኢትዮጵያ ምዕራባውያኑ የይሖዋ ምስክር ሚሲዮናውያን ከአገር ቢባረሩም በ1957 ዓ.ም. ከነበረው የአባላት ቁጥር በ1958 ዓ.ም. የዘጠኝ ሰዎች እድገት አሳይቶ ነበር[39]። ነገር ግን ይህ ቁጥር 1962 ዓ.ም. ወደ 76 [ከ128 ወደ 76] አሽቆዝቆ ነበር[40]። በ1962 ዓ.ም. ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር የነበራት ፌዴራሲዮን ስለተጠናቀቀ ኤርትራ የኢትዮጵያ ክፍለ አገር ሆነች። ይህም በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል የነበረው የሦስት አሥርተ ዓመታት ጦርነት አስከተለ። ይህ ነው እንግዲህ ለይሖዋ ምስክሮች የአባላት መመናመን ምክንያት የሆነው ከ1961 ዓ.ም. እስከ 1966 ዓ.ም. ምንም ዓይነት "መጠበቂያ ግንብ" መጽሔት በአማርኛ ቋንቋ አልታተመም። ዓመታዊ መጽሐፍም በኢትዮጵያ የነበሩትን የይሖዋ ምስክሮች ቁጥር አልገለጸም[41]። በ1964 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ከነበረው ችግር የተነሣ በኢትዮጵያ የነበረው ጉባዔዎችን የመቆጣጠር ሥራ ወደ ኬኒያው ቢሮ ተዘዋወረ።

ከ1960ዎቹ መካከል ጀምሮ የይሖዋ ምስክሮች አንጻራዊ ነጻነት ስላገኙ በየመንገድ ዳርም ሆነ የሰዎችን በር በማንኳኳት እምነታቸውን መስበክ ጀመሩ። በ1961 ዓ.ም. "እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን" [Let God Be True] በ1973 ዓ.ም. "ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራው እውነት" እንዲሁም "እውነተኛ ሰላምና ጥበቃ–ምንጭ የቱ ነው?" [True Peace and Security – From What Source?] የሚባሉት መጽሐፍት በአማርኛ ታተሙ። በትግረኛ ቋንቋ ደግሞ "የመንግሥት አደረጃጀት – ስብከትና ደቀ መዛሙርት ማፍራት" [Organization for Kingdom – Preaching and Disciple – Making] የሚባለው መጽሐፍ ተዘጋጀ።

ኢትዮጵያውያን የይሖዋ ምስክሮች ዓለማቀፋዊ ስብሰባዎችን የመካፈል ዕድል አገኙ። በ1969ዓ.ም ሠላሳ ሦስት የኢትዮጵያ ተወካዮች ፡– "ሰላም በምድር" [Peace on Earth] የተባለውን ጉባዔ በኔውዮርክና በለንደን ተካፈሉ[42]። በ1973 ዓ.ም. በኬኒያ "መለኮታዊ ድል" [Divine victory] የተባለውን ዓለማቀፋዊ ስብሰባ ጥቂት ኢትዮጵያውያን እንዲካፈሉ ተፈቀደላቸው። በአጠቃላይ አንጻራዊ ሰላሙ የይሖዋ ምስክሮች የመስክ አገልግሎት እንዲያካሂዱ፥ ጽሑፎቻቸውንና መጽሔቶቻቸውን እንዲያሠራጩ፥ ዓለማቀፋዊ ስብሰባዎችን እንዲካፈሉ ረድቶአቸዋል።

39. "የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ በኢትዮጵያና በኤርትራ ከ1951–1990" የሚለውን ርዕስ ይመለከቷል

40. Year book 1964, ገጽ 277-

41. "የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ" የሚለውን ርዕስ ይመለከቷል።

42. Year book 1970, ገጽ. 197



እነዚህ ዓመታት ለይሖዋ ምስክሮች ፍጹም የተመቹ ነበሩ ማለት አይቻልም። በአንዳንድ አካባቢዎች የይሖዋ ምስክሮች እንዳይሰብኩ በፖሊስ ታግደው ነበር። አንዳንዶች እገዳውን ቸል በማለት ለመስበክ በመሞከራቸው በወኅኒ ተጥለዋል። እሁድ ነሐሴ 27 ቀን 1972 ዓ.ም. ፖሊስ በአንዳንድ ጉባዔዎች በመሄድ 208 የይሖዋ ምስክሮችን አሠረ። ከእነዚህ ውስጥ 96ቱ ስድስት ወር ወኅኒ እንዲወርዱ ተፈረደባቸው። ነገር ግን አሥራቱ በገንዘብ ስለተለወጠ ገንዘቡን ከፍለው ተፈቱ። በ1971 ዓ.ም. በመንግሥት ባለሥልጣኖች ትእዛዝ በአስመራ የነበረው አጥቢያ የመንግሥት አዳራሽ ተዘጋ[43]።

አብዛኞቹ ችግሮች የተፈጠሩት በይሖዋ ምስክሮችና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መካከል በነበረው ችግር ነበር። በ1974 ዓ.ም. ብዙ የይሖዋ ምስክሮች ወኅኒ የወረዱት በስብከታቸው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ስለ ኀነታተሉ ነበር[44]። "ንቁ" በመባል የሚታወቀው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት መጽሔት በወቅቱ እንዲህ የሚል ጽሑፍ አሠራጭቶ ነበር፡– በቤተክርስቲያኒቱ መሬት ላይ ያለው አርሶ አደር ለመሬቱ ክራይ ቢከፍልም በከፍተኛ ሁኔታ በርሀብ እየተሰቃየ ነው[45]። በጊዜ የነበረውን ርሀብ ደግሞ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የትንቢት ፍጻሜ ተመልክቶ ነበር[46]።

ምንም እንኳ እስከ አሁን ያየነው የይሖዋ ምስክሮች በውጭ የተነሣባቸውን ችግር ቢሆንም፤ ውስጣዊ አለመግባባቶችም ተፈጥረውባቸው ነበር። በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት (የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት) የነበረው የጴንጤቆስጤ ልምምድ ወደ አጥብያ የይሖዋ ምስክሮች ጉባዔም ደርሶ ነበር። ስለዚህም አንዳንድ የይሖዋ ምስክሮች ሰማያዊ ተስፋ ተቀብለናል ማለት ጀመሩ [እንደ መጠበቂያ ግንብ ማኅበር አስተምህሮ ሰማያዊ ተስፋ የተቀበሉት "ቅቡዓን" ብቻ ናቸው]። ናይሮቢ ከሚገኘው ቢሮ ዊሊያ ኒስበት [William Nisbet] የተባለው ሚሲዮናዊ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ችግሩን ለመቅረፍ ቢሞክርም አንዳድ የይሖዋ ምስክሮች በአቋማቸው ስለጸኑ ከድርጅቱ ተባረዋል[47]።

43 Year book 1970 ገጽ.129-130

44 Year book 1975 ገጽ. 7-8

45 Awake 1974b, ገጽ. 30

46 Awake 1974a, ገጽ 7-8

47 Year book 1992, ገጽ. 130

## ሁለተኛው ስደት

የይሖዋ ምስክሮች ይጋጠማቸው ሌላው ስደት ከማርኪሲስታዊው መንግሥት ነው። በመስከረም 1974 ዓ.ም. በመፈንቅለ መንግሥት ደርግ ሥልጣን ጨበጠ። አገሪቱም በማርኪሲዝም – ሌኒኒዝም ሪኦተ – ዓለም መተዳደር ጀመረች። በ1970ዎቹ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናት፥ የይሖዋ ምስክሮችን ጨምሮ ታላቅ የሆነ ስደት ደረሰባቸው። እንደ 1960ዎቹ ከ1980 ዓ.ም. እስከ 1980 ዓ.ም. በዓመታዊ መጽሐፉም ሆነ "መጠበቂያ ግንብ" መጽሔት ምንም ዓይነት ስታቲስቲካዊ ዘገባ ያለመቅረቡ የዚህ ውጤት ነው[48]። እንደ 1992 ዓ.ም. ዓመታዊ መጽሐፍ ብዙ የይሖዋ ምስክሮች በእምነታቸው የተነሣ ተገድለዋል[49]።

## ማጠቃለያ

የክሪኮር ኢታዛኮርታዚያን ወራሾች ከ1991 ዓ.ም. ወዲህ ባሉት ዓመታት የየዓመቱ የእድገት መጠናቸው በአማካይ 15 በመቶ መሆኑ የሚያመለክተን እጅግ ስኬታማ መሆናቸውን ነው። በየዓመቱም አዲስ አበባ በሚገኘው የስፖርት መጫወቻ ሜዳ [ስታዲየም] አገር አቀፍ ስብሰባቸውን ያደርጋሉ። በ1997 ዓ.ም. ስታቲስቲክ መሠረት፡– 5,649 ንቁ ተሳታፊ አባላት፥ 5,292 ለመስክ 916 አቅኚዎች፥ 97 ጉባዔዎች፥ ለመስክ አገልግሎት 1,570 141 ሰዓት፥ 3,674 በቤት ውስጥ የተደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አሉአቸው።

ለይሖዋ ምስክሮች እድገት እንደ ምክንያት ከሚቆጠሩት መካከል በስደት ጊዜ ጸንተው መቆማቸው፥ ሊስብ የሚችሉና ወቅታዊ ርዕሶች ላይ የሚዘጋጁት ጽሑፎቻቸው፥ እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር መሠረት እምነቱን ማወቁ፥ አባላቱ እምነታቸውን ለሌላ ሰው ለማስተማር ያላቸው ከፍተኛ ፍላጎት እንደ ምክንያት ከሚቆጠሩት ውስጥ ዋንኞቹ ናቸው[50]።

---

48. የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ የሚለውን ርዕስ ይመለከቷል።
49. 1992 ዓመታዊ መጽሐፍ በደርግ ዘመን ስለ እምነታቸው የተገደሉትን ሰዎች ስምና ፎቶግራፍ አውጥቶአል።
50. አባላቱ የመጠበቂያ ግንብን አስተምህሮ የሚያስተምሩት እንዲሁም የድርጅቱን ጽሑፎች የሚያሠራጩት "የመስክ አገልግሎት" ለደኅንነታቸው አስፈላጊ (አንገብጋቢ) ስለሆነም ጭምር ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

# የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

3.1 የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የአምላክ ድርጅት ነውን? ... 50
3.2 የይሖዋ ምስክሮችና የአምላክ ስም ... 60
3.3 የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮተ ሥላሴ ... 74
3.4 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ... 92
3.5 ደኅንነት በይሖዋ ምስክሮች መንገድ ... 104
3.6 የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በሞት፥ በነፍስና በሲኦል ላይ ... 123
3.7 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት ... 132